> ሰማዕታት የዚህችን ዓለም ጣዕም በዕውነት ናቁ
> ደማቸውንም ስለ እግዚአብሔር አፈሰሱ።
> ስለመንግስተ ሰማያት መራራ ሞትን ታገሱ።
>
> ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ





**ስምዐ ጽድቅ**

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
<u>አዲስ አበባ</u>

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
ኮፒ አርታዒ፡-
ቀሲስ ልዑል ታመነ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# ቋሚ ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያንን ክብርና መብት ለማስከበር እንደሚሠራ አስታወቀ

*ካሳሁን ለምለሙ*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ክብርና መብት ለማስጠበቅ ቋሚ ቅዱስ ሲኖዶስ ከመቼውም ጊዜ በላይ በሰላማዊ መንገድ እንደሚሠራ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሕዝብ ግንኙነት መምሪያ አስታወቀ፡፡



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቋሚ ሲኖዶስ መስቀል ዐደባባይን፣ ጃንሜዳንና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎችን ጉዳይ በተመለከተ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ጋር ለመነጋገር ጥር ፳፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ይዞት የነበረውን ቀጠሮ ቋሚ ሲኖዶስ ተለዋጭ በማድረግ በቀጣይ በሚያስቀምጠው አቅጣጫና የጊዜ ቀጠሮ መሠረት ውይይቱ እንደሚካሄድ መምሪያው በመግለጫው አስታውቋል፡፡

የሕዝብ ግንኙነት መምሪያው አያይዞም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤተ ክርስቲያን በምታሳውቀው የጊዜ ቀጠሮ ለመወያየት ዝግጁ መሆኑን አስታውቆ፤ ቋሚ ቅዱስ ሲኖዶስም ከሚቀጥለው ቀጠሮ ጀምሮ ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ የቤተ ክርስቲያንን ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ጥረቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጧል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሁል ጊዜው ለመወያየትና አብሮ ለመሥራት በማንኛውም ሁኔታና ሰዓት ዝግጁ መሆኑን በማኅበራዊ ትስስር ገጹ አስታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ከተማ አስተዳደሩ ለውይይት ከመረጠው ቦታ ውጭ በጽርሐ መንበረ ፓትርያርክ ተገኝቶ ውይይት ለማድረግ ገቃደኛ አመሆኑን ማሳወቁ ይታወሳል፡፡

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሕክምና ማኅበር የነጻ ሕክምና አገልግሎት ሰጠ

*ምኒልክ ብርሃኑ*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሕክምና ባለሞያዎች ማኅበር ከማኅበረ ቅዱሳን ወልድያ ማእከል ሞያ አገልግሎት ክፍል ጋር በመተባበር በወልድያ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የነጻ ሕክምና አገልግሎት እንደሰጡ የሕክምና ማኅበሩ አስተባባሪ ዶክተር ዘላለም ይርጋ ገለጹ፡፡

ከጥር ፳፩-፳፪/፳፻፲፬ ዓ.ም ድረስ በነበራቸው የሁለት ቀናት ቆይታ በሆስፒታሉ ለተገኙ ታካሚዎች የውስጥ ደዌ ሕክምና፣ የልብ፣ የዐይን እና የሕፃናት ሕክምና እንዲሁም የሥነ አእምሮ ሕክምና ማድረጋቸው ዶክተር ዘላለም አስታውቀዋል፡፡

የሕክምና ማኅበሩ አስተባባሪ አያይዘውም የነጻ ሕክምና አገልግሎቱ በ፴፰ የሕክምና ባለሞያዎች አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰባ አምስት የኅብረተሰብ ክፍሎች ሕክምና እንደ ተደረገላቸው ገልጸዋል፡፡ ከሕክምና አገልግሎቱ በተጨማሪ የተለያዩ አልሚ ምግቦችን ድጋፍ እንዳደረጉም አክለው ገልጸዋል፡፡




የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሕክምና ማኅበር በጤናው ዘሪያ ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት በሚል ዓላማ የተቋቋመ ሲሆን ከቨርጂኒያ ከተማ ከሚገኘው “እኤም ለሀገሬ” በተሰኘ ግብረ ሠናይ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የነጻ ሕክምና እና የአልሚ ምግቦች ድጋፍ እንዳደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡




# መንግሥት ዜጎችን በእኩልነት የመምራት ኃላፊነቱን እንዲወጣ ተጠየቀ

*ካሳሁን ለምለሙ*

የኢትዮጵያ መንግሥት ሁሉንም ዜጎች ያለ ልዩነት በእኩልነት የመምራት ኃላፊነቱን እንዲወጣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮሳውያን የቤተ ክርስቲያን ክብርና መብት አስጠባቂ ኅብረት ባወጣው መግለጫ ጠየቀ።

ሕዝብ በተሰበሰበባቸው ዐደባባዮች ላይ ከመንግሥት ተወክለው ንግግር ለማድረግ የሚገኙ አካላት ለሁከትና ብጥብጥ የሚዳርጉ ንግግሮችን ከማድረግ እንዲቆጠቡ ያሳሰበው ኅብረቱ በመግለጫው ይህም የሃይማኖት እኩልነትን ያላከበረና አግላይ አካሄድ ነው ብሏል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ የሆኑት ወ/ሮ አዳነች አቤቤ በቅርቡ መስቀል ዐደባባይን በተመለከተ ያደረጉት ጠብ አጫሪ ንግግር የቤተ ክርስቲያንን መብት በግልጽ የሚጋፋና ለአንድ ወገን ያደላ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንን በይፋ ይቅርታ እንዲጠይቁ ኅብረቱ አሳስቦ በቀጣይ በቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች ላይ ለፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የሰጡትን ተመሳሳይ ፈቃድ ከመስጠትና ከፋፋይ ከሆነ ንግግራቸው እንዲቆጠቡ አሳስቧል።

በደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያንና በማኅደረ መለኮት ወይብላ ቅድስት ድንግል ማርያምና ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በኦርቶዶክሳውያን ላይ ጥቃት እንዲፈጽም ትእዛዝ የሰጡ፣ የፈጸሙና ጉዳት ያደረሱ የፀጥታና ሌሎች ተሳትፎ ያደረጉ አካላት ተለይተው ለፍርድ እንዲቀርቡ ኅብረቱ የጠየቀ ሲሆን መንግሥትም በጉዳዩ ዙሪያ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ማብራሪያ እንዲሠጥ ጠይቋል።

ኅብረቱ አክሎም በኦሮምያ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች "ሃይማኖታዊ ግጭት በማስነሣትና ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትን ለማስገደል መርተዋል፣ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ኦርቶዶክሳውያን ሞት ምክንያት ሆነዋል፣ በሺዎች ለሚቆጠሩ ኦርቶዶክሳውያን የአካል ጉዳት፣ስደትና መፈናቀል እንዲሁም በቢሊየን ለሚቆጠሩ የቤተ ክርስቲያንና የኦርቶዶክሳውያን ሀብትና ንብረት ውድመት ምክንያት ሆነዋል" ያላቸውን ተጠርጣሪዎች ክስ ማቋረጥ ተገቢ እንዳልሆነ ገልጦ መንግሥት ጉዳያቸውን እንደገና እዲመለከት አስታውቋል።

በመጨረሻም በምዕራብ ኦሮምያ ኦርቶዶክሳውያን በሃይማኖታቸው ብቻ ተለይተው እየተፈጸመባቸው ያለውን ግድያ፣ እንግልትና ማፈናቀል መንግሥት እንዲያስቆም ኅብረቱ ጠይቋል።

# የህልውና ጉዳይ ነው!

በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተካሄደ ያለው ዘርፈ ብዙ ፈተና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ እና ሥር እየሰደደ በመምጣቱ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና እየተፈታተነ ይገኛል። ትላንት ቤተ ክርስቲያንን የዘር ካባ አልብሶ የአንድ ብሔር ሃይማኖት አድርጎ ያስቀመጣት መጥፎ ትርክት ለዘመናት ከማትወጣው ችግር ውስጥ ከቷታል። ይህ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሉዓላዊነቷ እንዲሸረሸር፣ መብቷ እንዲሸራረፍ ምክንያት ሆኗል። ይህ በዕኩይ ትርክት የተሸፈነ ኦርቶዶክስ ጠል ሥውር ዘመቻ ለዘመናት የተከበረ ቅጥርዋን ከመነቅነቅ አልፎ ቀስ በቀስ አጥርዋን እስከ መነቃቀል ደርሷል።

በቤተ ክርስቲያን የውስጥ አሠራር ጣልቃ መግባት፣ አባቶችን መከፋፈል፣ ምእመናንን በሃይማኖታቸው ብቻ ከኖሩበት ሀገር እና መንደር ማፈናቀል፣ ቤተ ክርስቲያን ላይ ጉዳት ማድረስ፣ መዝረፍ፣ ማቃጠል፣ ማጥፋት እንደ ዓላማ ተይዞ እየተሠራ ነው። በየዘመናቱ በሀገር ውስጥ በደረሱ የተለያዩ ጥፋቶች ምክንያት ሁል ጊዜም እየተጠቃች ያለችው ይህቺ አንጋፋ ቤተ ክርስቲያን ናት። የቅርብ ጊዜውን ከ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በሀገሪቱ ላይ የተፈጸሙት እና እየተፈጸሙ ያሉትን ክስተቶች ማጤን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በተለያየ መንገድ የጥቃት ሰለባ እየሆነች እንደሆነ ለመረዳት ብዙም የሚያዳግት አይደለም።

በተለያየ ጊዜና ወቅት አባቶች፣ ማኅበራት፣ የሰንበት ት/ቤቶች፣ የቤተ ክርስቲያን አካላት የሆኑ ሁሉ ከግለሰብ እስከ ማኅበር፤ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ በተደጋጋሚ እንዳነሡት ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተደረገ ያለው መዋቅራዊ የጥፋት ዘመቻ በአንድ ቀን የበቀለ ወይም የተከሰተ ሳይሆን ግብ ተኮር እኩይ ዓላማን ያነገበ ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን እየቀያየረ እና ጡንቻውን እያፈረጠመ የመጣ የጠላት ዒላማ ነው። ሆኖም ሃይማኖትን የብሔር ጭምብል አልብሶ በሐሰት ትርክት መሸፈን፣ መዋቅር ዘርግቶ እና ሆን ብሎ በግለሰቦች ጀርባ ታዝሎ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት መሞከር ሀገርን ማጥፋት መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል።

ይህ አንድን ግርግር ተከትለው፣ ሀገር ላይ የሚከሰቱ የተለያዩ ሁነቶችን በተለይም የቤተ ክርስቲያንን በዓላት ጠብቀው የሚፈጠሩ ጥቃቶች ‹ግርግር ለሌባ ያመቻል› እንዲሉ ድንገት የሚከሰቱ ሳይሆኑ ሆን ተብሎ፣ አጀንዳ ተቀርጾላቸው፣ ጊዜ ተቀምሮላቸው እና ስያሜ ተሰጥቶአቸው ወቅትና ቦታ ለይተው የሚፈነዱ ቦንቦች መሆናቸውን ሁሉም ከልብ ሊገነዘበው ይገባል። ጥቃቶች ኦርቶዶክስ ተኮር ናቸው ሲባል በመሰለኝ የሚነገር ሳይሆን ጥቃቶች የሚፈጸሙት በቤተ ክርስቲያን ዐበይት በዓላት መሆናቸው፣ ብዙዎች በተለያየ መንገድ የኦርቶዶክስ የሆኑ ይዞታዎች ላይ ዓይናቸውን መጣላቸውና በልዩ ልዩ መንገድ ሊነጥቋት መታገላቸው በቂ መረጃዎች ከመሆናቸውም በላይ የዐደባባይ ምሥጢርም ናቸው።

የሀገራችን ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፲፭ ‹‹ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው። ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም።›› የሚል የዜጎችን በሕይወት የመኖር መብት ቢደነግግም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ የሆኑ ምእመናን በሃይማኖታቸው ምክንያት ከአካባቢያቸው፣ ከኖሩበት ሀገር ሲፈናቀሉ፣ ሀብት ንብረታቸው ሲወድም እና ሲዘረፍ፣ ሲገደሉ ቆይተዋል ዛሬም ጥቃቱ አላቆመም።

በቤተ ክርስቲያን ላይ የተፈጸመው የትላንቱ ግፍና ሰቈቃ ሳያበቃ ዛሬም ታቦት አጅበው በሚሄዱ ምእመናን በታቦቱ ፊት በጭካኔ ሲገደሉ ማየት የሀገራችን ሕገ መንግሥት ለየትኛው አካል ነው የቆመው? የሚል ጥያቄን ይፈጥራል። በተመሳሳይ መንገድ ሲከወን የመጣው እንዲህ ዓይነቱ ከሀገር ሕግ ጋር የሚጣላ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ሲፈጸም ከዚህ በፊት ይሆን እንደነበረው በአንድ ሰሞን ጩኸት ብቻ የሚያበቃ እና ነገሩ ካለፈ በኋላ ‹‹የውሾን ነገር ያነሳ ውሾ ይሁን››

እንደሚባለው የአንድ ሰሞን ብቻ መሆን የለበትም። ትላንት በየአካባቢው፣ በየክልሉ ኦርቶዶክስ ስለሆኑ ብቻ የተገደሉ ዛሬም እየተገደሉ ያሉ ብዙዎች ናቸው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖታቸው ምክንያት መስዋዕትነትን የተቀበሉትን ክርስቲያኖች የዘመናችን ሰማዕታት መሆናቸውን ታምናለች የክብር ሥፍራም ትሰጣቸዋለች።

ሆኖም በምድራዊ ሕግ እንደ አንድ ባለ አገር በተሰጠው የመኖር ሕግ እንዳይኖር ተደርጎ ሲገደል ሕይወቱን የነጠቀው አካል መዋቅሩን ተከትሎ በሕግ አግባብ የሚጠየቅበት እንዲሁም እስከ መጨረሻው ክትትል የሚደረግበት መዋቅራዊ ሥርዓት መዘርጋት ከቤተ ክርስቲያን አካላት ይጠበቃል። ቤተ ክርስቲያንን እና ተከታይ ምእመናንዋን ለማጥፋት፣ ለማጥቃት ፊት ለፊት እየተካሄደ ያለውን ኦርቶዶክስ ጠል የጥፋት ዘመቻ ፊት ለፊት መቃወም ዘመኑ የሚጠይቀው መንፈሳዊ ትግል ነው።

ሀገር ከውስጥ እና ከውጭ ጠላት ሲነሣባት ከፊት ቀድማ የምትገኝ፤ ዜጎች ተከባብረው በአንድነት እንዲኖሩ የምትሰብክ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ በጠላትነት የምትፈረጅበት መጥፎ ትርክት ሊቆም ይገባል። አባቶቻችን እስከ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እና በተከታይ ምእመናን ላይ የሚፈጸመውን ግፍ እና ሰቈቃ እያዩ ከትላንት ነገ በጎ ነገር ይመጣል በማለት ነገሮች የሚሻሻሉ፣ ሀገር ሰላም እንዲሆን የሄዱበት የጥበብ እና የትእግሥት መንገድ እንደፈሪ አሊያም እንዳላዋቂ ሊያስቈጥራቸው አይገባም። ቤተ ክርስቲያን ሀገርን ከውጭ ወራሪ ስትጠብቅ፣ ታቦት ይዛ እስከ ጦር ግንባር እየዘመተች ጠላት ድል ስታደርግ እንድነበር ማንኛውም አካል ሊዘነጋው አይገባም። ለሀገር ያበረከተችው ውለታ ተዘንግቶ በቤተ ክርስቲያን ላይ እጅን ማንሳት ትላንትን አለማወቅ፤ ታሪክንም መዘንጋት ነው። እንዲህ ዓይነቱን የተሳሳተ መንገድ የማረም የማስተካከል ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቀደመ ሉዓላዊነት መመለስ ከሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጅ ይጠበቃል።

ሥርዓቱ የፈጠረው ኦርቶዶክስን የማዳከም ሥውር ሤራ ኦርቶዶክሳዊም ሆነ ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል በጥብቅ ሊያወግዘው ይገባል። የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሆነው ቤተ ክርስቲያን እና ምእመናን በምትገፋባቸው ጉዳዮች ላይ ባለመተባበር የቤተ ክርስቲያን ልጅነታቸውን ሊያሳዩ ይገባል።

በአጠቃላይ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉና ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሥት አገልጋዮች በተለያየ መዋቅር ውስጥ የሚገኙ የሥራ ኀላፊዎች ኀላፊነታቸው ለሕዝብ ነውና ሁሉን በእኩል ዓይን በማየት ቢያገለግሉና ነገ የማይወቀሱበትን ሥራ ሊሠሩ ይገባል። ሆን ብለው የያዙትን ኀላፊነት ተገን በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን በብዙ መንገድ ለማጥፋት የሚጥሩ ሁሉ ከእንዲህ ዓይነት ታሪካዊ ጥፋት እና ስሐተት ሊቆጠቡ ይገባል። በቤተ ክርስቲያን ላይ እየተካሄደ ያለው ሥር ሰደድ የጥፋት ዘመቻ በቤተ ክርስቲያን ሕልውና ላይ የመጣ ነውና አጀንዳ ይዘው እና ቀርጸው ለሚንቀሳቀሱ አካላት አጀንዳ ቀርጾ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ተገቢም ነው እንላለን።

# የምእመናን ዜግነታዊ መብቶች ይከበሩ፤ የቤተ ክርስቲያንም ሉዓላዊነት ሳይሸራረፍ ይረጋገጥ!!

ክፍል አንድ

ሻምበል ጥላሁን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ መሠረትነት ላይ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በፈተና ውስጥ እያለፈች አሁን ካለንበት ዘመን ደርሳለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን መልኩን እና ሁኔታውን እየለዋወጠ እየተከሠተ የሚታየው ጦርነት፣ የምእመናን በክርስትናቸው ምክንያት መገደል፣ የቤተ ክርስቲያን መቃጠል፣ የምእመናን መሰደድ እና ሀብት ንብረታቸው መዘረፍ እጅግ ልብን የሚሰብር እና ከመቼውም በላይ የቤተ ክርስቲያንን ልዕልዕና የሚጋፋ እየሆነ መጥቷል፡፡

በተለይም ከ፲፱፻፺ዎቹ ጀምሮ ሁለንተናዊ የአስተሳሰብ ውጊያ ሲደረግባት ቆይቷል፡፡ ይህ የአስተሳሰብ ውጊያ በጊዜ ሂደት መዋቅራዊ ወደመሆን እያደገ ሄዶ አሁን ያለንበት ወቅት ላይ ደርሰናል፡፡ በነዚህ ረጅም ዓመታት ውስጥ ሲካሄድ የቆየውን ጥቃት ማሳያ የሆኑ በርካታ ክሥተቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተለይ የመንግሥትን ለውጥ ተከትሎ በሀገሪቱ በርካታ ስፍራዎች የአምልኮ ቦታዎች መነጠቅ፣ ሕዝበ ክርስቲያኑ የዐደባባይ አምልኮ ሥርዓቱን በአግባቡ እንዳይፈጽም በጥቂት ባለ ሥልጣናት ትእዛዝና በጥቂት ሕግ አስከባሪዎች የሚደርሰው ውክቢያ ይሻሻላል ተብሎ ሲጠበቅ እየባሰና የተለያዩ ኦርቶዶክስ ተኮር ጥቃቶች ሲፈጸሙ ይታያል፡፡ በዚህም ተከታታይ ጽሑፍ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሱ ጥቃቶችንና ጥቃቶቹን ተከትሎ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ ከማኅበራት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከመንግሥትና ከዲሞክራሲ ተቋማት የተሰጡ መግለጫዎችንና አስተያየቶችን በዝርዝር እናቀርባለን፡፡

የመንግሥትን ለውጥን ተከትሎ ከ፳፻፲፩ አጋማሽ እስከ ፳፻፲፬ ዓም በቤተ ክርስቲያን ላይ እየተከሠቱ ያሉ ችግሮች፦

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሀገራዊ አንድነት ለሀገረ መንግሥት ግንባታና ለሕዝቦች የጋራ እድገት ጉልህ ድርሻ የነበራትና ያላት፣ በዚሁ አበርክቶዋ ዘመናትን የምትሻገር፣ በክርስቶስ ደም ላይ የተመሠረተች፣ በሕዝቦች አንድነት ላይ ጽኑ እምነትና መሠረት ያላት የሀገር ባለውለታ እንደሆነች ሊካድ የማይቻል ሐቅ ነው፡፡ ነገር ግን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የኢትዮጵያን አንድነት ከማይሹ አካላት ለፖለቲካ ትርፍ በማሰብ የቤተ ክርስቲያንን ሊደበዝዝና ሊሻር የማይችል ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለዘመናት ሕያው ምሥክር የሆኑ አገልግሎቶቿን ለመገዳደር እና በተለያየ መንገድ ስም በማጥፋት ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ታላቅ ባለውለታ በሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሱ ያሉ ፈተናዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በዐይነት እና በመጠን እየጨመሩ መጥተዋል፡፡

በአንድ በኩል ልጆቿና አገልጋዮቿ ሰበብ እየተፈለገላቸው ያለወንጀላቸው ንብረታቸው እየወደመ፣ ለዘመናት ከኖሩበት ቀያቸው ተፈናቅለው የከፋ ኑሮ መኖራቸውና ቊጥራቸው ቀላል የማይባሉት ደግሞ እንደ በግ እስከመታረድ ደርሰዋል፡፡ በሌላ በኩል ከይዞታዎቿ መነጠቅ ጀምሮ ንዋየ ቅድሳቷ እና ሕንፃ ቤተመቅደሷን እስከ መዘረፍ፣ ማውደም እና ማቃጠል የሚደርስ ከፍተኛ በደል እያስተናገደች ትገኛለች፡፡

ይህ ሁሉ በደልና ግፍ ጊዜና ቦታ ሳይለይ ከጠረፍ እስከ ጠረፍ የሚከናወን ሲሆን ችግሮቹ በተከሰቱባቸው አካባቢዎች አፋጣኝ ሕግን የማስከበር ርምጃ ባለመወሰዳቸው በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍሎች በሚከናወኑ የተቃውሞም ይሁን የድጋፍ እንቅስቃሴዎች ቤተ ክርስቲያንን መዝለፍ፣ ምእመናን ላይ ጉዳት ማድረስ ዘረፋና ማቃጠል የመሳሰሉ ድርጊቶች እንደ ተገቢ ርምጃዎች እየተወሰዱ መጥተዋል፡፡ በነዚህ ሂደቶች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን መዋቅር የሕግ ይከበር ጥያቄዎችን በይፋ ከማቅረብ በዘለለ ለሀገራዊ ሰላም መምጣት ሲባል በትእግሥት ማለፍ እንደ አማራጭ ተወስዷል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ጥቃቶች ጨመሩ እንጂ አልቀነሱም፡፡

በተለይ የመንግሥትን ለውጥ ተከትሎ ሚያዝያ ፳፻፲፩ ዓ.ም ሐረር ሳሮሙጢ በሚኖሩ በአራት ካህናትና በምእመናን ላይ የመግደል ሙከራ ተደርጕ ከባድ ድብደባ ተፈጽሞባቸው በእግዚአብሔር ቸርነት ተርፈው ሆስፒታል መግባታቸው ተገልጾ ነበር፡፡ በዚህ ድርጊት አጥፊዎች ተገቢውን ቅጣት ባለማግኘታቸው ጥቃቱ በድሬዳዋ፣ በከሚሴ፣ በኤፍራታና ግድም፣ በሰሜን ሸዋ ሰላሌ፣ በምዕራብ ሸዋ፣ ወሊሶ፡ በጅማ ሊሙኮሳ በተከታታይ የተፈጸሙትን ወንጀሎች በተለይ ሕይወት የቀጠፉና ንብረት ያወደሙ ጥቃቶች የሚዘነጉ አይደሉም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች በ፳፻፲፪ ዓ.ም ቀጥሎ ፖለቲከኞች በቀሰቀሱት ግጭት ጠንሳሽ ንግግር እስከ ፳፻፲፪ ዓ.ም አጋማሽ ብቻ ፹፮ ያህል ክርስቲያኖች በተለያየ መንገድ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል፡፡ ይህን ተከትሎ ቅዱስ ፓትርያርኩና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት መንግሥት ችግሩን እንዲያስቆም የሚከተለውን መልእክት ማስተላለፋቸው ይታወሳል፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ

ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት በጥቅምት ፲፪ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም በተካሄደው የቅዱስ ሲኖዶስ የመጀመሪያ ዓመታዊ የምልዓተ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የመክፈቻ ቃለ ምዕዳን ባስተላለፉት መልእክት "በቤተ ክርስቲያን ላይ በቀጣይነት እየደረሰ ያለውን ተጽዕኖ እና ጥቃት ለማስቆም፣ የመንጋው እረኞች የሆኑ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ድምፃቸውን በዓለም ዙሪያ በአንድነት ለማሰማት እና እስከ ሞት ድረስ መሥዋዕት ለመክፈል እንዲዘጋጁ" አሳስበው ነበር። ቅዱስነታቸው በመክፈቻ ቃለ ምዕዳኑ "የመንግሥት የበታች መዋቅር እና ባለሥልጣናት በምእመናን ላይ እያደረሱት ያለው ግፍ ቤተ ክርስቲያን ከምትታገሠው በላይ እየሆነ መጥቷል" ማለታቸውም አይዘነጋም።

በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠውን የእምነት ነፃነት በሚሸረሽሩ የታችኛው መዋቅር ባለሥልጣናት ላይ መንግሥት የማያዳግም የማስተካከያ ሥራ እንዲሠራ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ሲል ብትጠይቅም፣ የአብያተ ክርስቲያን ቃጠሎ፣ የካህናት እና ምእመናን መፈናቀል እና ግድያ ስጋቶች መኖራቸውን በወቅቱ በተካሔደው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በቀረቡ የአህጉረ ስብከት ሪፖርቶች ማረጋገጥ መቻሉን ቅዱስነታቸው ጠቅሰው ነበር። አያይዘውም "ነባር የቤተ ክርስቲያናችን ይዞታዎች ሥልጣንን መከታ ባደረጉ ወገኖች እየተነጠቁ ነው፤ ምእመናን በሚደርስባቸው የማያባራ ተጽዕኖ እና አድልዎ ከቀዬአቸው እየተፈናቀሉ እና እየተሰደዱ ነው" ያሉት ፓትርያርኩ "እንዲህ ዓይነቱ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት እስከ መቼ ነው የሚቀጥለው?" በማለት ጠይቀዋል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰውን የጥቃት እና የተጽዕኖ ድርጊት ለማስቆም የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ በሙሉ አቅማቸው መሥራት እና በዓለም ዙሪያ መደመጥ በሚችሉበት አኳኋን መነሣሣት እንዳለባቸው፤ ከዚህም አልፈው እስከ ሞት ድረስ መሥዋዕት መሆን እንደሚጠበቅባቸው በወቅቱ ያሳሰቡት ቅዱስነታቸው "ይህ ድርጊት እንዲቆም እስከ ሞት ድረስ መሥዋዕት መሆን ከዚህ ጉባኤ አባላት ይጠበቃል። ይህ ጉባኤ የኀያሉ የእግዚአብሔር ጉባኤ ነው፤ ይህ ጉባኤ በኢትዮጵያ ብቻ ከሰባ ሚሊዮን ያላነሰ ሠራዊት ያለው ጉባኤ እንጂ ብቻውን አይደለም፤ ይህ ጉባኤ በሙሉ አቅሙ ሥራውን ከሠራ እና ድምፁን ካነሣ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ሰሚው ብዙ ነው" ማለታቸውም ይታወሳል።

መብታችንን ለማስከበር መንግሥትን በተደጋጋሚ ከመጠየቅና የባለሥልጣናቱን የተሳሳቱ አካሔዶች በቅርበት እየተከታተሉ በማያዳግም ርምጃ እንዲያስተካክል ከማድረግ ጋራ ሁል ጊዜም በተጎጂው ሕዝብ መካከል እየተገኘን በልዩ ልዩ ግፍ ልባቸው የተሰበረውን የልጆቻችንን ኀዘን መቅረፍ ይኖርብናል፤ ችግራቸውንም መጋራት ይጠበቅብናል፤ የተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናትን እንደገና መገንባት አለብን በማለት ቅዱስ ፓትርያርኩ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳቱን በወቅቱ ማሳሰባቸውም አይዘነጋም።

የምእመናን ዜግነታዊ መብቶች እንዲከበሩ እና በመሪዎች ቅስቀሳ ከሚደርስባቸው ጥቃት እንዲጠበቁ ቅዱስ ሲኖዶስ አጥብቆ መጠየቅ እንዳለበት የስዊድንና አካባቢው ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ አሳስበው ነበር። ብፁዕነታቸው በዚሁ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የመክፈቻ ጸሎት መርሐ ግብር ላይ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክተው ሲናገሩ "የመሪዎች የቅስቀሳ ቃል በክርስቲያኖች ላይ እየተባባሰ ለመጣው ጥቃት አንዱ መንሥኤ ነው›› ያሉ ሲሆን ‹‹ መሪዎች ከአንደበታቸው በሚወጣ የቅስቀሳ ቃል ክርስቲያኖችን ለግድያ እና መፈናቀል እየዳረጉ በመሆናቸው ከንግግራቸው ተቆጥበው እና ሰላምን ሰብከው ከልመና ያወጡት ዘንድ ልናርማቸው ይገባል።›› ማለታቸው ይታወሳል።

እንደ ቤንሻንጉል ጉምዝ ያሉት አካባቢዎች ከዐሥርት ዓመታት በፊት የጥይት ድምፅ የማይሰማባቸው እንደነበሩ በወቅቱ በሰጡት ትምህርት ያስታወሱት ብፁዕነታቸው ዛሬ ሰላማቸውን እያጡ የሚገኙት የሕዝብን አንድነት እና ኅብረት በሚያበላሽ የአንደበት እሳት በመሆኑ መሪዎች በሰላም ማስሪያ ቃል አካባቢውን አውቀው እንዲጎበኙት፤ ይልቁንም ምእመናን ሕግ በሚፈቅድላቸው ቦታ ተዘዋውረው ለመኖር እና ለመሥራት መሰቀል እና መገደል በማለት አጽንኦት ሰጥተዋል።

ቤተ ክርስቲያንን የማሳደድ፣ ጠላሸት የመቀባት እና ስም የማጥፋት ዘመቻ ዘመናትን ያስቆጠረ እንደሆነ ቢታወቅም እንደዚህ ዘመን የከፋ ጊዜ በዕድሜያቸው አለማየታቸውን እና አለመስማታቸውን የገለጹት ብፁዕነታቸው ‹‹ስደቱ እና መከራው የሚያበረታን እንጂ ጠላቶቻችን እንደሚመስላቸው የሚያደክመን አይደለም፤ ሆኖም ቤተ ክርስቲያን ‹ለምን ይህ ሆነ?› ብላ በመጠየቅ ለምእመናኗ ደኅንነት መጠበቅ መሟገት፤ ልጆቿንም ‹አይዟችሁ፤ ብላ ማጽናናት አለባት›› ሲሉም አሳስበው ነበር።

ቤተ ክርስቲያን ችግሮቹ ተባብሰው ወደ ለየለት የእርስ በእርስ ግጭት እንዳያመሩ ምእመናኖቿን እያረጋጋች መንግሥት አጥፊዎቹን በመቅጣት ችግሩን እንዲፈታ በትዕግሥት ብትጠይቅም ጥቃቶቹ እየተባባሱ ወደ ፳፻፲፫ ዓ.ም መሻገራቸው አልቀረም። ነሐሴ ፲፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር በሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ፀረ ሰላም ኃይሎች በፈጸሙት ጥቃት በርካታ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ለሞትና ለስደት መዳረጋቸው የማኅበረ ቅዱሳን ብሮድካስት አገልግሎት ተቋም እና የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ. የቴሌቪዥን ሚዲያዎች በወቅቱ ዘግበውት ነበር።

በወቅቱ የምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት የሃይማኖት አባቶች “መንግሥት የቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን ደኅንነት ያስጠብቅ” በሚል ርእስ ባወጡት መግለጫ ጥሪ አቅርበው ነበረ፡፡

በሀገሪቱ ውስጥ የተፈጠረውን ቀውስ ተከትሎ በቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ያለውን ዝርፊያ፣ ቃጠሎና ውድመት በእጅጉ ያሳሰባቸው እነዚህ አባቶች በመግለጫቸው “ወቅታዊ የሀገሪቱን የፖለቲካ ቀውስ እንደመልካም አጋጣሚ ተጠቅመው ቤተ ክርስቲያን ችግር ውስጥ እንድትወድቅ የሚፈልጉ አንዳንድ ፀረ ሰላም ኃይሎች በእኩይ ድርጊታቸው ቤተ ክርስቲያንን ከፍተኛ አደጋ ላይ ጥለዋታል” ሲሉ ተናግረዋል፡፡ መንግሥት የምእመናንና የአብያተ ክርስቲያናትን ሰላምና ደኅንነት የመጠበቅ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባም በወቅቱ ለመንግሥት ጥሪ አስተላልፈው ነበር፡፡

በተጨማሪም በክልሉ በተለያዩ የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ ኃላፊዎች ቤተ ክርስቲያን እና በምእመናን ላይ እየደረሰ ያለውን ዘርፈ ብዙ ችግር ሰምተው እንዳልሰሙ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ማለፋቸውን አስመልክቶ “በሀገረ ስብከቱ ሥር ለችግር የተጋለጡ አብያተ ክርስቲያናትንንና ምእመናንን ለመኅብኘት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የደኅንነት ድጋፍ እንዲያደርግልን ጥያቄ ብናቀርብም እስካሁን ድረስ ምላሽ አላገኘንም” ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበው እንደነበርም ይታወሳል፡፡ ሆኖም ቤተ ክርስቲያን በምእመናን ልጆቿ አንደበት ለጮኸችው ጩኸት እና ላቀረበችው ጥሪ ምላሽ የሰጣት ወይም ለችግሩ መፍትሔ ያቀረበላት አካል አልነበረም፡፡

ችግሮቹ መባባሳቸው ቤተ ክርስቲያን የሞቱባትን ካህናትና ምእመናን፣ የወደሙባትን አብያተ ክርስቲያናትና የጠፉባትን ንዋያተ ቅድሳት ለማጣራት ችግር ሆኖ እንደቆየ በተለይም የምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት አካባቢ የጦርነት ቀጠና ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአካባቢው በተፈጠረ የፀጥታ ችግር ምክንያት ሀገረ ስብከቱ ወደ ወረዳው አጣሪ ልዑክ መላክ አልቻለም፤ ይሁን እንጂ ወረዳ ቤተ ክህነቱ የችግሩን ጥልቀትና ስፋት ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ለጠቅላይ ቤተ ክህነትና ለሀገረ ስብከቱ ማሳወቁን በመግለጫቸው ጠቅሰው ነበር፡፡

ከዓመት ዓመት ራሱን እየቀጠለ የመጣው ቤተ ክርስቲያንን የማዳከም ብሎም የማጥፋት ዘመቻ አንድ ጊዜ በብሔር ሌላ ጊዜ በሃይማኖት ጥላ ሥር ሆኖ ቤተ ክርስቲያን እና ምእመናን በሰቆቃ እንዲቆዩ አድርጎአቸዋል፡፡ በተለይ ፳፻፲፫ ዓ.ም በምሥራቅ ሐረርጌ ጎሮ ጉቱ ወረዳ፣ በምዕራብ አርሲ-ዶዶላ እና ኮፈሌ፣ በባሌ ሮቤ እና ድሬዳዋ፣ የብሔርና የሃይማኖት አክራሪዎች ካደረሷቸው አሠቃቂ ግድያዎች ባሻገር፣ የምእመናንን መኖርያ ቤቶች፣ ልዩ ልዩ ንብረቶችና የንግድ ተቋሞች፣ ሙሉ በሙሉ በመዝረፍና በማቃጠል የተነጣጠረ ጥቃት መፈጸማቸውን ጥቅምት ፳፬ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ቅዱስ ሲኖዶስ ጉዳዩን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ መገለጹ ይታወሳል፡፡

በዚህም ጥቃት በሺዎች የሚቆጠሩ ምእመናን ከቀዬአቸው ተፈናቅለው፣ በአብያተ ክርስቲያንና በሌሎች ጊዜአዊ መጠለያዎች ለመሰንበት መገደዳቸው አይዘነጋም፡፡ በዶዶላ ምዕራፈ ቅዱሳን አቡነ ገብረ ክርስቶስ እና ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን፣ ከ፴ሺህ ፴፻ በላይ የሆኑ ምእመናን ከቤተ ሰቦቻቸው ጋራ ተጠልለው መሰንበታቸው በወቅቱ በማኅበረ ቅዱሳን፣ እንደ በጴጥሮሳውያንና እንደ ሐራ ተዋሕዶ ድኅረ ገጽ መገለጹ ይታወቃል፡፡

በነዚህ ዘገባዎች የወረዳው ቤተ ክህነት ጽ/ቤት መኖርያ ቤቶቻቸው፣ ልዩ ልዩ ንብረቶቻቸው፣ የንግድ ተቋሞቻቸውና ድርጅቶቻቸው የ፻፵፫ ምእመናን ንብቶች መዘረፋቸውና የቀሩት መቃጠላቸውን፣ በምሥራቅ ሐረርጌ ጎሮ ጉቱ ወረዳ መንዲሳ ቀበሌ ጋንጌሶ፣ ዴራ እና ቡራክሳ ጎጦች እንዲሁም በካራሚሌ እና ባሮዳ፣ ከ፻፹፱ በላይ አባወራዎች ንብረት ሙሉ በሙሉ መዘረፉንና ምእመናን ለእንግልትና መፈናቀል መዳርጋቸው በወቅቱ ተጠቅሷል፡፡

በተለይ በቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ላይ እየደረሰ ያለውን ግድያና ስደት ተከትሎ ማኅበረ ቅዱሳን “ቤተ ክርስቲያን ስደት ላይ ናት” ሲል ግንቦት ፫ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም መግለጫ ማውጣቱም አይዘነጋም፡፡ “ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከ፲፱፻፺ዎቹ ጀምሮ ሁለንተናዊ የአስተሳሰብ ውጊያ ሲደረግባት ቆይቷል” የሚለው የማኅበሩ መግለጫ ‹‹ይህ የአስተሳሰብ ውጊያ በጊዜ ሂደት መዋቅራዊ ወደ መሆን እያደገ ሄዶ አሁን ካለንበት ወቅት ላይ ደርሰናል፤ በነዚህ በርካታ ዓመታት ውስጥ ሲካሄድ የቆየውን ጥቃት ማሳያ የሆኑ በርካታ ክሥተቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡›› ሲል አስረድቷል፡፡

ከዚሁም ጋር አያይዞ “ባለፉት ዓመታት በየአካባቢው የሚደረጉ የክርስቲያኖች በክርስቲያንነታቸው ተለይተው መገደል መሰደድ የአብያተ ክርስቲያናት መቃጠልና የምእመናን ሀብትና ንብረት መዘረፍ የማንነትዋ መገለጫ የሆኑት ሀብቶችዋን ከዳር እስከ መሀል የመቀማትና የማጥፋት ብሎም ለሌሎች አካላትና አገልግሎቶች እንዲውሉ መደረጉ ሌላኛው ዓይነተኛ ማሳያ ነው›› ሲል ማኅበሩ በመግለጫው አንሥቷል፡፡

# “መምህራኑ በሱስንዮስ ዘመን የከሸፈውን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ካቶሊክ የማድረግ ተልዕኮ ወስደው የመጡ ነበሩ”

**አቶ ከፈለኝ ኀይሉ**

ካሳሁን ለምለሙ

*ክፍል ሁለት*

***የተወደደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ቀጣዩንና ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ እነሆ***

**ስምዐ ጽድቅ፡- የሰንበት ትምህርት ቤቱ የተለየ የሚባል አሠራር ምን ነበረ? የአባላት የእርስ በእርስ ግንኙነትስ ምን ይመስል ነበር?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** ተምሮ ማስተማሩ ጠንካራ የሚባል የአሠራር አደረጃጀት ያለው በመሆኑ የተለየ የሚያደርገው ጥብቅ በሆኑ መመሪያዎችና ሥነ ሥርዓቶች የሚመራ በመሆኑ ነው። የመዝሙር ክፍል፣ የኪነ-ጥበብ፣ የስብከተ ወንጌል፣ የጸሎት፣ ነዳያንን የመርዳት አገልግሎትና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶችንም ጭምር ያማከለ አሠራር አለው። አደረጃጀቱም ሁሉንም የማኅበሩን አባላት ያሳተፈ ነው። አደረጃጀቱ የተፈጠረውም ከዛሬ ኀምሳ ዓመታት በፊት ጀምሮ ነው።



*አቶ ከፈለኝ ኃይሉ በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ተምሮ ማስተማር ሰንበት ትቤት የሥራ አመራር ቦርድ አባል*

**ስምዐ ጽድቅ፡- ዐረፍተ ዘመን የገታቸው የተምሮ ማስተማር መሥራቾችና አባላት ለማኅበሩ የነበራቸው አስተዋጽኦ ምን ነበር?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** ተምሮ ማስተማሩን ከመሠረቱት ሰዎች መካከል ቀሲስ ታደሰ መንግሥቱ ሲሆኑ ሌላው ደግሞ ክብር አቶ አበበ ከበደ ነበሩ። እኒህ የተከበሩ ሰው በደርግ ዘመነ መንግሥት ከእነ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጋር ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ተገድለዋል።

ክቡር አቶ አበበ ከበደ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር መልካም ሥራ ሠርተዋል። ለሠሩት ሥራ በሀገርም በቤተ ክርስቲያንም ደረጃ መታሰቢያ ያልተደረገላቸው ሰው ናቸው። መልካም ሥራቸው እንዲሁ እየተነገረ ይኖራል። ክቡር አቶ አበበ ከበደ የተለያዩ ፋብሪካዎችና የሥራ ቦታዎች እንዲቋቋሙና የአካል ጉዳተኞች ሠርተው ራሳቸውን እንዲችሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ነበሩ። ሌላውና የማይረሳ አሻራቸውን አሳርፈው ያለፉት ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ናቸው። ብፅዕነታቸው የተምሮ ማስተማርን ሰንበት ት/ቤት ከመሠረቱት አባቶች መካከል የመጀመሪያው ሲሆኑ መምህር፣ አባትና ባራኪ፣ የተምሮ ማስተማር የበላይ ጠባቂና መኩሪያ የነበሩ አባት ናቸው። ተምህሮ ማስተማርና ብፁዕነታቸው የማይነጣጠሉ ነበሩ። ብፁዕነታቸው የአርሲ ሀገር ስብከት ሊቀ ጳጳስ በነበሩበት ወቅትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በተጨማሪም እነ ገብረ ጊዮርጊስ አጋዤ፣ መምህር ግርማ ከበደ፣ መምህር ላቀው አዲሳ የመሳሰሉት ለተምህሮ ማስተማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱ አባቶች መካከል በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱ ናቸው።

**ስምዐ ጽድቅ፡- የተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት ውስጣዊ ችግሮች ምን ምን ነበሩ?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** መንፈሳዊ አገልግሎት ሁልጊዜም ቢሆን ከፈተናዎች የጸዳ አይሆንም። ተምህሮ ማስተማርም ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ፈተናዎችን አሳልፏል። ሰንበት ትምህርት ቤቱ የራሱ የሆነ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ያልነበረው በመሆኑ አባላት ተሰብስበው ለመወያየት በእጅጉ ይቸገሩ ነበር። የተስተካከለ አደረጃጀት ያለመኖሩ ሌላው የተምህሮ ማስተማሩ ፈተና ሲሆን በየጊዜው ምስካየ ኅዙናን ለማስተዳደር ከሚመጡ አባቶች ጋር ያለው አንዳንድ አለመግባባትም ሌላኛው የአገልግሎት ፈተና ነበር። የመናፍቃን እንቅስቃሴ በተምህሮ ማስተማር ባይከሰትም በገዳሙ የተከሰተበት ወቅት ነበር። በወቅቱ ቅዳሴ ‹‹በፒያኖ›› ይቀደስ የሚሉ አካላት በነበሩበት ወቅት ተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤቱ ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጎ አስቀርቶታል። በአንዳንድ ከባድና ጥቃቅን ችግሮች ምክንያት አባላቶች በነፃነትና በፍላጎት መንገድ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳይሰጡ አድርጓቸዋል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በዚህ ወቅት የተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤቱ ምን ዓይነት አገልግሎት እየፈጸመ ይገኛል? ሌሎች ሰንበት ትምህርት ቤቶችስ ከተምህሮ ማስተማሩ ምን ሊማሩ ይገባል?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** ተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት በትምህርት ዙሪያ በአራት የትኩረት መስኮች የአምስት ዓመት ስልታዊ ዕቅድ ነድፎ እየሠራ ይገኛል:: አራቱ የትኩረት መስኮች የምንላቸው መማር፣ ማወቅ፣ ማስተማር እንዲሁም ማጽናት ሲሆኑ በዚህ መሠረት መስማት ለተሳናቸው፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸውና ተምረው ማስተማር ለሚፈልጉ ሁሉ መንፈሳዊ ትምህርት ይሰጣል:: ትምህርቱ የሚሰጠው እንደየዕድሜ ደረጃቸው ሲሆን ለሕፃናት፣ ለታዳጊዎችና ለአዋቂዎች ብሎ በመመደብ የሚሰጥ ነው:: በገጽ ለገጽ ትምህርታቸውን መከታተል ለማይችሉ አካላት ደግሞ የርቀት መርሐ ግብር ተመቻችቶላቸዋል:: መምህራንን በተለያዩ ቦታዎች መመደብና የመምህራን እጥረት ባሉባቸው የሀገራችን ክፍሎች ጭምር በመዘዋወር ብርሃን የሆነውን ወንጌል ሰንበት ትምህርት ቤቱ እያስተማረ ይገኛል::

በተጨማሪም በተለያዩ የበጎ አድራጎት ሥራዎች ይሳተፋል:: ለነዳያን ምግበ ሥጋ ብቻ ሳይሆን ምግበ ነፍስን ጭምር እንዲያገኙና በሥጋ ወደሙ እንዲወሰኑ የማበረታታትና የማስተማር ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል:: መስማት የተሳናቸው ወገኖች በራሳቸው የምልክት ቋንቋ ለንስሐ አባታቸው እንዲናዘዙና ሥጋ ወደሙ እንዲቀበሉ ያደርጋል:: በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ መስማት የተሳናቸው ሰዎች ክህነት ተቀብለው እንዲያገለግሉ አድርጓል:: ሰንበት ትምህርት ቤቱ አገልግሎቱን የሚመራው በማንዋል ሳይሆን በዲጅታል ቴክኖሎጂ በመሆኑ ሃይማኖትን እንደአባቶቻችን፣ ጥበብን እንደጊዜያችን እያዳረሰ ይገኛል::

በአጠቃላይ ሰንበት ትምህርት ቤቱ በተለያዩ መስኮች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ያለና ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት እየፈጸመ ያለ ነው:: ሌሎች ሰንበት ትምህርት ቤቶች ከዚህ ሰንበት ትምህርት ቤት በርካታ ቁም ነገሮችን ሊማሩ ስለሚችሉ በፈለጉት ጊዜ መጥተው መጎብኘት ይችላሉ:: ሰንበት ትምህርት ቤቱ የመንፈሳዊ አገልግሎት መስጫ መጻሕፍት ያሉት ሲሆን የራሱ የሆነ ትምህርት የሚሰጥበት ሥነ ዘዴ ያለው ነው:: በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የትምህርት ማንዋሎች ተዘጋጅተዋል:: ስለሆነም ሌሎች ሰንበት ትምህርት ቤቶች ተምህሮ ማስተማር ያለውን ገጸ በረከት መጠቀምና ማየት ይችላሉ::

ለአንዲት ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እድገት ሰንበት ትምህርት ቤቶች የእርስ በእርስ ልምድ ልውውጥ ቢያደርጉ መልካም ነውና ተምህሮ ማስተማሩን ሌሎች ሰንበት ትምህርት ቤቶች ሊወስዱትና ሊማሩበት የሚገባው ቁም ነገር ስለሚኖር የልምድ ልውውጥ የማድረግ ፍላጎትም አለው::

**ስምዐ ጽድቅ፡- የተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤቱ ያሉበት ወቅታዊ ችግሮችና መልካም አጋጣሚዎች ምን ምን ናቸው?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** የመጀመሪያው ችግር ሰንበት ትምህርት ቤቱ በቂ የሆነ የመገልገያ ግብአቶችና ሕንጻዎች ያለመኖሩ ነው:: ሌላው ወጣቶችና ሌሎች የሰንበት ትምህርት ቤቱ አባላት ከሰንበት ውጭ በሌሎች ቀናት ጭምር በሰንበት ትምህርት ቤቱ በመንፈሳዊ አገልግሎት የሚሳተፉባቸው ቀናት ውስን መሆኑ ነው:: አንዳንድ አባላት በግል ጉዳይና በመሰል ችግሮች ከአገልግሎት የመቅረትና የተሳታፊዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣት ለተፈለገው አገልግሎት ፈተና ሆኗል:: ሰንበት ትምህርት ቤቱ በቀላል ሁኔታ ስብከተ ወንጌልን እንዲያስተምር ዲጅታል ቴክኖሎጂው መልካም አጋጣሚ ሆኗል:: በማኅበራዊ ሚዲያ ጥሩ አጋጣሚ በመፈጠሩም ሰንበት ትምህርት ቤቱ በመረዳት የተፈጠረውን አጋጣሚ በተገቢ መንገድ እየተጠቀመበት ይገኛል:: ሰንበት ትምህርት ቤቱ ከገዳሙ አባቶች ጋር ተግባብቶና ተሳስሮ መሥራቱም ለተቀላጠፈ አገልግሎት በር ከፍቶልናል:: ሰንበት ትምህርት ቤቱም ለገዳሙ በዕውቀት በጉልበት የሚጠበቅበትን እያደረገ ይገኛል::

**ስምዐ ጽድቅ፡- የሰንበት ትምህርት ቤቱ የገቢ ምንጭ ምንድን ነው?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** ሰንበት ትምህርት ቤቱ ከገዳሙ የተወሰነ ገቢ ያገኛል:: ከገዳሙ የሚገኘው ገቢ ሰንበት ትምህርት ቤቱ ካለው ሰፊ አገልግሎት አንጻር ላይበቃው ቢችልም ተጨማሪ በጀት ከመደበኛ አባላቱ ተሰብስቦ የሚገኘው ገቢ ለአገልግሎት የተወሰነ ድጋፍ ያደርጋል:: በመላው ዓለም ያሉ የሰንበት ትምህርት ቤቱ አባላት የሚያዋጡት ወርኃዊ መዋጮ ለሰንበት ትምህርት ቤቱ ትልቅ አቅም ፈጥሮለታል:: ሌላው ደግሞ ከሚቀረጹ የተለያዩ ፕሮጀክቶችና የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብሮች አማካይነት የሚገኝ ገቢ አለ:: ሎተሪን ጨምሮ ሌሎች የገቢ ማስገኛ

ምንጮችን በመጠቀም ሰንበት ትምህርት ቤቱ የመንፈሳዊ አገልግሎቱን የሚያግዝ ገቢ ይሰበስባል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- የተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤቱ ምን ያህል አባላት እንዳለውና የአባላቱ ትስስር ምን እንደሚመስል ቢገልጹልን።**

**አቶ ከፈለኝ፡-** ሰንበት ትምህርት ቤቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አባላት ያሉት ሲሆን አንድነትና ትስስራቸው ደግሞ ይበል የሚያሰኝ ነው። በእድርና በተለያዩ አደረጃጀቶች ውስጥ በመሳተፍም የመረዳዳት ባህላቸውን ያጎለበቱ ናቸው። የአባላቱን አንድነት ለማጠናከርም መንፈሳዊ ጥማቸውን ለማርካት ተከታታይ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ይሰጣል። በተጨማሪም በሰርግ፣ በለቅሶ በተለያዩ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ አባላት ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ። በጓደኝነት በመንፈሳዊ አጋርነት ያላቸው መተሳሰብና ቁርኝት በጣም ከፍተኛ ነው። በውጭ ያሉ አባላት ከዚያው ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ በተጨማሪ ሰንበት ትምህርት ቤቱንና ቤተ ክርስቲያንን በክህሎታቸው፣ በዕውቀታቸውና በገንዘባቸው እያገዙ ይገኛሉ።




*በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ተምሮ ማስተማር ሰንበት ትቤት*

**ስምዐ ጽድቅ፡- የሰንበት ትምህርት ቤቱ የወደፊት ግብ ምንድን ነው?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** ሰንበት ትምህርት ቤቱ በየአምስት ዓመቱ በሚተገበረው ስልታዊ ዕቅድ የአብነት ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ እንዲሰጥ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። የአባላቱ የጸሎትና የመንፈሳዊ ሕይወት ጽናት እያደገ እንድሄድ የማድረግ ሥራዎች በቀጣይ ይሠራሉ። ክርስትና በሚለው መርሕ መሠረት የተቸገሩ ወገኖችን መርዳትና የተቃጠሉና የወደሙ አብያተ ክርስቲያናትን መልሶ የመገንባት ሥራዎች ይሠራሉ። የአገልጋይ አባቶት ኑሮ እንዲሻሻልም የበኩሉን ድርሻ ይወጣል። አንዳንድ ጽንፈኛ ኃይሎች በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ እያደረጉ ያለውን በደል ለመመከት አባላትንና አጠቃላይ ሕዝበ ክርስቲያኑን የማንቃት ሥራ እንሠራለን። ምእመናንም ለመንግሥተ ሰማያት እንዲበቁ የማስተማር የማበረታታት ሥራ ይሠራል። ከጠቅላይ ቤተ ክህነት በሚመጣ መመሪያ መሠረትም ሥርዓት ለማስከበር የማኅበሩ አባላት የአካልና የሥነ ልቡና ዝግጅት እንዲያደርጉ ሥራ እንሠራለን።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት ጥናት አጥንተዋል፤ ጥናቱን ለማጥናት ምን አነሣሣዎት? በጥናቱ የተገኘው ግኝትስ ምንድን ነው?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** ጥናቱ የተጠናው የተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት የስልሳኛ ዓመት የምሥረታ በዓልን መሠረት አድርጎ ነው። በተለያየ ምክንያት የማኅበሩን አመሠራረትና ምንነት የሚገልጽ ወይም የሚያስረዳ ጥናታዊ ጽሑፍ ባለመኖሩ ምክንያት ጥናት ላጠና ችያለሁ። የተለያዩ ጥናቶች ባይኖሩም በአንዳንድ ግለሰቦች አማካይነት የተጻፉ መጻሕፍት ነበሩ፤ ነገር ግን መጻሕፍቱ ስለ ተምህሮ ማስተማር ገላጭ ባለመሆናቸውና በተጠበቀው ልክ ባለመገኘታቸው ሁሉንም መጻሕፍቶች ካነበብኩ በኋላ ጥናት አጥንቻለሁ። የጥናቱ ግኝት ያመለከተውም ተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት የተመሠረተው ‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የተጣሉትን ለማስታረቅ›› በሚል ሐሳብ ሳይሆን በወቅቱ በተፈሪ መኮንን አዳሪ ትምህርት ቤት ያስተምሩ የነበሩ ካቶሊካውያን ያደርጉት የነበረውን ሃይማኖታዊ ቅሰጣ ለመከላከል መሆኑን ነው።

**ስምዐ ጽድቅ፡- አቶ ከፈለኝ ጥያቄያችን ጨርሰናል፤ ስለነበር ቆይታ በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን።**

**አቶ ከፈለኝ፡-** እኔም እዚህ ድረስ መጥታችሁ ቃለመጠየቅ ስላደረጋችን በተምሮ ማስተማር ስም አመሰግናለው።

# “ምእመናን በየአጥቢያቸው እየተገናኙ መምከራቸው አካባቢው ከሞላ ጎደል ከከፋ መከራና እልቂት መትረፍ ችሏል”

ሊቀ ኅሩያን ኃይሉ ዓለሙ

በዲ/ን አሻግሬ አምጤና በካሳሁን ለምለሙ

በሀገራችን አንዳንድ አካባቢዎች በተከሠተው ጦርነት ውድ የሆነው የሰው ሕይወት ጠፍቷል፤ሀብት ንብረትም ወድሟል፡፡ ጦርነቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአብያተ ክርስቲያናትና በምእመናን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡ ይህ ጉዳት ከደረሰባቸው አህጉረ ስብከት መካከል የዋግኸምራ ሀገረ ሰብከት አንዱ ሲሆን በሀገረ ስብከቱ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትና ምእመናን የግፍና የመከራ ጊዜ አሳልፈዋል፡፡ በዚያ የግፍና የመከራ ጊዜያት “በጎቻችንን ጥለን የትም አንሄድም” ያሉ ጠንካራና አረአያ የሆኑ አባቶች ተፈጥረዋል፡፡

በወቅቱ እንዚህ የሃይማኖት አባቶች የምእመናንና የአብያተ ክርስቲያናት ድኅንነት እንዲጠበቅ፤በሕክምና፣በመድኃይኒት እጦትና በምግብ እጥረት ማኅበረሰቡ እንዳይታመምና እንዳይሞት የበኩላቸውን ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በዚያ የመከራ ጊዜ ውስጥ እውነተኛ የበጎች እረኛ፣ አጽናኝና መካሪ ሆነው ከቆዩት የሃይማኖት አባቶች መካከል የወግኸምራ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ሊቀ ኅሩያን ኃይሉ ዓለሙ አንዱ ሲሆኑ ዝግጅት ክፍላችን ከእርሳቸው ጋር አጭር ቆይታ አድርጓል፡፡ ያደረግነውን ቆይታም እንደሚከተለው አቅርበነዋል፤መልካም ንባብ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ በዋግኸምራ ሀገረ ስብከት በርካታ ችግሮች ተከሥተዋልና ችግሮቹን ለማለፍ ሀገረ ስብከቱ ምን ተግባራን ሲያከናውን ቆየ?**

**ሊቀ ኅሩያን ኃይሉ ዓለሙ፡-** በሀገረ ስብከታችን ከጦርነቱ ጋት ተያይዞ ችግሮች የተፈጠሩት ከነሐሴ ወር ፳፻፲፬ ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን የመንግሥት መዋቅር ባለመኖሩም ቤተ ክርስቲያናችን የመንግሥትን ድርሻ ወስዳ ስትሠራ ቆይታለች፡፡ በተለይ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ በርናባስን ጨምሮ ሌሎች አገልጋዮች የዋግኸምራ ሀገረ ስብከትን የሕወሓት ታጣቂዎች ከተቆጣጠሩት በኋላ ከአመራሮቹ ጋር በሰላምና በፀጥታ ዙሪያ ውይይት አድርገናል፡፡

የውይይቱ ዓላማ ታጣቂዎቹ በሀገረ ስብከቱ ያሉ ንፁሃን የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ አላስፈላጊ ጥቃትና እንግልት እንዳይፈጽሙ ለማሳሰብ ነው፡፡ የሕውሓት ሠራዊት በንብረትና በሰው ሕይወት ላይ ውድመትና ጥፋት እንዳይፈጽም የጦር አመራሮቹ ታች ድረስ ወርደው ሠራዊታቸውን እንዲያስተምሩና እንዲመክሩ የማድረግ ሥራ የተሠራ ሲሆን ይህም መልካም የሚባል ውጤት አምጥቷል፡፡ በሀገረ ስብከቱ የነበረው የጸጥታ ሁኔታ ከታጣቂዎቹ ጋር በነበረው መግባባት እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም የአካባቢውን ኅብረተሰብ ከፍተኛ የሆነ የረሀብ አደጋ ፈትኖታል፡፡ ለአጭር ጊዜ የዘለቀው ዘረፋና ውንብድናም ለአካባቢያችን ሌላ የራስ ምታት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ዝርፊያና ነጠቃው ኅብረተሰቡ እንዲማረርና ለአባቶች አቤቱታ እንዲያሰማ አድርጓል፡፡ ሌላ የሀገረ ስብከታችን ፈተና ሆኖ የቆየው መሠረታዊ የሆነ የጤናና የመድኃኒት አቅርቦት ችግር ነው፡፡



ሊቀ ኅሩያን ኃይሉ ዓለሙ

ችግሩን ለመቅረፍ ከስደት የተረፉ የጤና ባለሙያዎችን በማስተባበር ወደ ሥራ ገበታቸው ለመመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ብዙ ዘመን ያስቆጠሩና የአካባቢን ሚዛን የሚጠብቁ ሀገር በቀል ዛፎች እንዳይወድሙ

*ሥራ መሠራት እንዳለበት ከኅብረተሰቡ በተሰጠን ጥቆማ መሠረት ማኅበረሰቡን ያካተተ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ ኮሚቴው በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የበላይነት የሚመራና ተጠሪነቱም ለሀገረ ስብከቱ ሆኖ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ ተግባሩም አላግባብ የሆነ የደን ጭፍጨፋን አስቀርቷል፡፡ ሌሎች ችግሮችም በአካባቢው እንዳይፈጠሩ የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዳይዘረፉና ውድመት እንዳይደርስባቸው ቤተ ክርስቲያን የአካባቢውን ባለሀብቶች በማስተባበር ደሞዝ የሚከፈላቸው የጥበቃ ሠራተኞች እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ እስካሁን ድረስ በጥበቃ ላይ ያሉ ተቋማት መንግሥት ርክክብ አላደረገባቸውም፡፡*

በጤናው ዘርፍም ፹፱ የጤና ባለሙያዎችንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በአካባቢያቸው ተረጋግተው እንዲቆዩና ለኅብረተሰቡ የተለመደ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጡ አድርገናል፡፡ የሕክምና ባለሙያዎቹ የተጠናከረ ሥራ በመስጠታቸውም ፵፷፻፴ በላይ ምእመናን በቂ የሆነ የሕክምና አገልግሎትና ክትትል አግኝተዋል፡፡ አገልግሎቱ ተጠናክሮ በመቀጠሉ እሰካሁን ድረስ በሞት አፋፍ ላይ የነበሩ ፷፫ ነፍሰጡር እናቶች በቀዶ ጥገና እንዲወልዱ ተደርጓል፡፡ የተሰጠው ቀልጣፋ የሕክምና አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን የታደገችበት አንዱ መልካም ተግባር ነው፡፡ በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ለማገዝ ከተለያዩ የአካባቢው ባለሀብቶች የገንዘብ ብድር ወስዳለች፡፡ በገንዘብ እጦት ምክንያት ብድሩንም እስካሁን ድረስ ለባለሀብቶቹ አልመለሰችም፡፡ የተቸገሩ ምእመናንን ከመርዳት አንጻር የገጠር አብያተ ክርስቲያናትና ገበሬዎች ያላቸውን እህል ድጋፍ አድርገዋል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በአካባቢው የነበረውን ችግር በመረዳዳትና በጥበብ ለማለፍ ተችሏል፤ችግሮችን በጥበብ፣ በመደጋገፍና በመረዳዳት ለማለፍ በቀጣይ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ሊቀ ኅሩያን ኃይሉ፡-** በችግሩ ምክንያት በኅብረተሰቡ መካከል የነበረው መረዳዳትና መተጋገዝ በቀጣይ ተጠናክሮ መቀጠል መቻል አለበት፡፡ ከራስ በላይ ለሌሎች የሚሉ በጎ አመለካከቶች ሊጎለብቱ ይገባል፡፡ ሰውነት ሊቀድም ይገባል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን የሀገረ ስብከቱ አካባቢዎች ወደ ነበሩበት ለመመለስና የወደሙ ሀብትና ንብረቶችን ለመተካት ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ሊቀ ኅሩያን ኃይሉ፡-** የተፈናቀሉ ምእመናን ጉዳይ፣ የተቃጠሉና የወደሙ አብያተ ክርስቲያናትና የመንግስት ተቋማት ጉዳይ እጅግ አሳሳቢዎች ናቸው፡፡ ይህንን አሳሳቢ ጉዳይ ለማስተካከል ሁሉም ኢትዮጵያዊ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡ እንደ ሀገረ ስብከት በአካባቢው የደረሰውን ውድመትና በትክክል ሰንዶ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ የሚገባን ነው፡፡ ጉዳዩን ወደሚመለከተውን አካል ከማድረስ በተጨማሪ በማኅበረሰቡ መካከል የታየውን የመረዳዳትና የመተጋገዝ መንፈስ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የማስተማር፣ የማንቃትና የማስገንዘብ ሥራ መሥራት አለብን፡፡ እነዚህ መልካም የሆኑ ማኅበረሰባዊ እሴቶች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ተከታታይ የሆነ ትምህርት ከእኛ ከአባቶች ይጠበቃል፡፡ ከእኛና ከአካባቢው ማኅበረሰብ ውጭ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ በአካባቢው ያለውን ጉዳት በአካል መጥቶ በመረዳት መወሰድ ላለባቸው የድጋፍ ርምጃዎች የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ መንገዱን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ወቅት በዋግኽምራ አካባቢ ያሉ የአብነት ትምህርት ቤቶች አደጋ ላይ ይገኛሉ፡፡ በትምህርት ቤቶቹ ያሉ ተማሪዎች በኢኮኖሚ እየተጋገዙ ወቅቱን ቢገፉም መምህራኖቹ ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች ስለገጠማቸው የአብነት ትምህርቱ ተቋርጧል፡፡ መምህራን ወደተለያየ አካባቢ በመሰደዳቸው ተማሪዎቹ እርስ በርሳቸው ሲማማሩ ቆይተዋል፡፡ ወቅቱ የአብነት ተማሪዎች ለምነው የሚበሉበት ጊዜ አይደለምና የቤተ ክርስቲያንም ሆነ የምእመናን የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ጠቅላይ ቤተ ክህነት በተጎዱ አካባቢዎች ላይ የተጠናከረ ጥናት በማድረግ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ላለው ከመጨመር ይልቅ ለሌላው ማገዝ ያስፈልጋል፡፡

በባንኮች አገልግሎት ማቋረጥና በገንዘብ እጥረት ምክንያት ከሀገረ ስብከት እስከ አጥቢያ ድረስ ያሉ አገልጋዮች ለበርካታ ወራቶች ደመወዝ ሳይከፈላቸው ቆይቷል፡፡ እነዚህንና መሰል ችግሮችን ለመለየት የመንግሥት አካላት በኮሚቴ ደረጃ እንቅስቃሴ እያደረጉ ቢሆንም ከቤተ ክርስቲያን በኩል ለጉዳዩ የተሰጠው ትኩረት ግን አናሳ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አካባቢው በሰላምና መረጋጋት ውስጥ በነበረበት ወቅት ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ከሚያገኘው ዓመታዊ ገቢ በመቶኛ ቀንሶ ይሰጥ የነበር ነው፡፡ አሁን ደግሞ ችግር በገጠመውና ከግለሰቦች ገንዘብ ተበደሮ የነፋስ አድን ሥራ ሲሠራ በመቆየቱ በከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገኛል፡፡ በችግር ውስጥ

ያለውን ሀገረ ስብከት ጠቅላይ ቤተ ክህነቱ የችግሩን መጠን አጥንቶ ተገቢ የሚለውን ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳንን ጨመሮ ሌሎች ማኅበራትም የተጎዱ አህጉረ ስብከቶች በተገቢ ሁኔታ በመመልከት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሚዲያዎችም ተገቢ  የሚዲያ ሽፋን ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ችግሮች በሚዲያ መገለጥ ከጀመሩ ማኅበረሰቡን የሚረዱ አካላት ከየአቅጣጫው ይገኛሉና የሚዲያ አጠቃቀማችን ከተፈለገው ደረጃ  በላይ መሆን አለበት፡፡ መንግሥት ለአካባቢው እየሰጠው ያለውን ትኩረት አጠናክሮ በመቀጠል ለዜጎች አስፈላጊውን ሁሉ የሰብአዊና የፀጥታ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ግብረሰናይ ድርጅቶችም በረሀብና በሕክምና እጦት ለሚሠቃየው ወገናችን ሊደርሱለት ይገባል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ በርናባስ በችግሩ ወቅት ሕዝቡን ባያረጋጉና ባያጽናኑ ኖሮ በአካባቢው ምን ዓይነት ችግር ይፈጠር ነበረ?**

**ሊቀ ኅሩያን ኃይሉ፡-** ብፁዕ አባታችን በሀገረ ስብከታቸው ተወስነው መቆየታቸው በሕዝበ ክርስቲያኑና በንብረት ላይ ሊደርስ የነበረውን ከፍተኛ ጥፋት አሥቀርቷል፡፡ አብያተ ክርስቲያናትም አገልግሎታቸው እንዳይታጎል የራሱ ድርሻ ነበረ፡፡ ብፁዕአባታችን አጠቃላይ በሀገረ ስብከቱ ላሉ ወገኖች ኃይልና ብርታት ነው የሆኑት፡፡ እርሳቸው በአካባቢው ተገኝተው የማረጋጋት፣ የማፅናናት ሥራ ባይሠሩና ከታጣቂዎቹ ጋር ምክክር ባያደርጉ ኖሮ በአካባቢው የከፋ ውድመት ይደርስ ነበረ፡፡ አባቶቻችን የመንጋው እረኞች ናቸውና ብፁዕነታቸው እውነተኛ ሰብሳቢ መሆናቸውን በተግባር አሳይተዋል፡፡

ከብፁዕነታቸው አባታዊ ተጋድሎ በተጨማሪ በየአጥቢያው በአገልግሎት ላይ የነበሩ ካህናት አባቶች ሕዝበ ክርስቲያኑን ከማረጋጋትና አገልግሎታቸውን ከመፈጸም አንፃር አባታዊ ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል፡፡ ሕዝቡ በፍርሃት ቆመን ተሞልቶ አካባቢውን ጥሎ በሚሸሽበት ወቅት ካህናት አባቶች ቀን ምእመናንን በማጽናናት ሌሊት ድግሞ በማኅሌቱ ተግተው ያገለግሉ ነበረ፡፡ ካህናት ያለደመወዝ ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ ከራሳቸው ድሉት ይልቅ የማኅበረሰቡ ችግር ዕለት ዕለት ያሳስባቸው ነበር፡፡ ቁርጠኛ ካህናት ያሉት ቁርጠኛ ሊቀ ጳጳስ በመኖራቸው ነው፡፡ እርሳቸው ባይኖሩና አባታዊ አመራር ባይሰጡ ኖሮ በረሃብ፣ በበሽታ እንዲሁም በጦርነቱ የሚሞተውና የሚሰደደው የኅብረተሰብ ክፍል ቍጥር በጣም ከፍተኛ ይሆን ነበረ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ቀረ የሚሉትና ማመስገን የሚፈልጉት አካል ካለ?**

**ሊቀ ኅሩያን ኃይሉ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ ሁሉን ላደረገልን እግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል፡፡ በመቀጠል የብፁዕነታቸውን የርዳታ ጥሪ ተቀብለው ያለ የሌላቸውን ጥሪት አምጥተው ድግፍ ላደረጉ የአካባቢው ተወላጅ ባለሀብቶችና በጎ አድራጊዎች አካላት ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ ፈታኝ ወቅት በነበረበት ወቅት ባለሀብቶች የኅብረተሰቡንና የመንግሥት ሠራተኛውን ችግር አቃለዋል፡፡ በቀጣይ ሀገር ሰላም ሲሆን ለእነዚህ አካላት የምስጋና መርሐ ግብር ይዘጋጃል፡፡

ሌላው ከመስከረም ፳፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ የኮሚቴ አባላትን ማመስገን ይገባል፡፡ አብዛኛዎቹ የኮሚቴ አባላት የሀገር ሽማግሌዎችና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ናቸው፡፡ መፍትሔ በማፈላለግና የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ከፖለቲካና ከጦር አመራሮች ጋር በጋራ እየተመካከሩ ከፍተኛ የሆነ የነፍስ አድን ሥራ ሠርተዋል፡፡ መፍትሔ በማፈላለግ የደከመው ኮሚቴው ላበረከተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ምስጋና ይገባዋል፡፡ የሰቆጣ ከተማ አስተዳደርና በዙሪያው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ላበረከቱት ድጋፍ ከፍተኛ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና የአካባቢው ኅብረተሰብ ቁና እህል ሰፍረው አምጥተው፡፡ ይህ ድጋፍ የብዙ ሰዎችን ሕይወት ታድጎልናል፡፡ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ሕዝበ ክርስቲያን ገንዘብ አዋጥተው ልከውልናል፡፡ እህል በዱቤ የሰጡንን  ባለሀብቶችን ጭምር ልናመሰግናቸው ይገባል፡፡ ድጋፍ ያደረጉልንና ለማድረግ አስበው ሁኔታዎች ያልፈቀዱላቸውን አካላት ሁሉ እናመሰግናለን፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ለነበረን ቆይታ እግዚአብሔር ይስጥልን፡፡**

**ሊቀ ኅሩያን ኃይሉ፡-** እኔም የማውቀውን እንዳካፍላችሁ ለቃለ መጠይቁ ስለጋበዛችሁኝ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ፡፡

# ጥር ፳፩ የእመቤታችን በዓለ ዕረፍት፤ አስተርእዮ ማርያም

ምኒልክ ብርሃኑ

ሰላም ለእናንተ ይሁን ልጆች! እንደምን አላችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን እኛ በጣም ደኅና ነን። በባለፈው ቆይታችን ስለ ጥምቀት በዓል በደንብ ተምረናል። ታዲያ ልጆች! እናንተስ የጥምቀትን በዓል እንዴት አከበራችሁ?

ጠበል በመረጨት፣ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ታቦት በማክበር፣ መዝሙር ከሰንበት ትምህርት ቤት ዘማርያን ጋር በመዘመር እንዳከበራችሁ ተስፋ እናደርጋለን። በዓሉንም እንዲህ አድርጋችሁ ካከበራችሁ በረከትን አግኝታችኋል። ምክንያቱም በዓላትን የምናከብረው በረከትን እና ደስታን ለማግኘት ስለሆነ ነው።

ልጆች! ዛሬ ደግሞ የምንማረው ስለ አስተርእዮ ነው። በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ መሠረት አሁን ያለንበት ወቅት ዘመነ አስተርእዮ ይባላል። ዘመነ አስተርእዮ ምን ማለት እንደሆነ፣ ለምን ዘመነ አስተርእዮ እንደተባለ፣ በዘመነ አስተርእዮ ጊዜ ስለሚከበረው የእመቤታችን በዓል አጠር አድርገን እንማራለን። አብራችሁን እንድትቆዩ እየጋበዝን መልካም ንባብ እንዲሆንላችሁ እንመኛለን።

ልጆች! አስተርእዮ ቃሉ አስተርአየ ታየ፤ ተገለጠ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጕሙም መታየት፣ መገለጥ ማለት ነው። አስተርእዮ የሚባለው ዘመን ደግሞ ከልደት ጀምሮ እስከ ነነዌ ጾም መግቢያ ባሉት ወቅት ነው።

ታዲያ ልጆች! ይህ ወቅት ዘመነ አስተርእዮ የተባለበት ምክንያት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ በሥጋ የታየበት እና የተጠመቀበት፤ የሥላሴ አንድነት እና ሦስትነት በዮርዳኖስ ወንዝ የተገለጠበት በመሆኑ ዘመነ አስተርእዮ ይባላል። በተለይ ደግሞ ለእኛ ለልጆች በጣም ደስ የሚለን ወቅት ነው። ምክንያቱም አዳዲስ ልብስ ለብሰን፣ አምረን ተውበን የገና በዓልን እና የጥምቀት በዓልን የምናከብርበት ጊዜ በመሆኑ ነው።

ሌላው ደግሞ ልጆች! በጥር ወር በታላቅ ድምቀት የሚከበር ታላቅ በዓል አለ። ይህ በዓል አስተርእዮ ማርያም ወይም የእመቤታችን በዓለ ዕረፍት ይባላል። አስተርእዮ ማርያም የተባለበት ምክንያት በዓሉ በጥር ወር ስለሚከበር ነው። ታዲያ ይህ በዓል የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍትን ታሳቢ በማድረግ የምናከብረው በዓል ነው። የሚከበረው ደግሞ ጥር ፳፩ ቀን ነው፤ ከዚህ በታች እንደሚከተለው በዓሉ የሚከበረብትን ምክንያት እንማራለን ማለት ነው፤ በጥሞና ተከታተሉ።



የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍት

ልጆች! እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዚህ ዓለም የኖረችው ስልሳ አራት ዓመት ነው። ታዲያ እመቤታችን ሁል ጊዜ ጠዋትም ማታም ጸሎት ታደርግ ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን ጸሎት እያደረገች እያለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመላእክት ታጅቦ ቅድስት ድንግል ማርያም ወዳለችበት

ሥፍራ መጣና እንዲህ አላት፤

“እናቴ ሆይ! ከዚህ ዓለም ድካም ላሳርፍሽ መጣሁ” አላት፡፡

እርሷም “ልጄ ሰማይና ምድር የማይወስኑህን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀኔ ወስጄ በድንግልና ወልጄህ እንዴት እሞታለሁ? አለችው፡፡

ታዲያ ልጆች! በዚህ ጊዜ አንድ ነገር ተከሠተ፡፡ እርሱም በዚያ ከተማ ይኖሩ የነበሩ አይሁድ ሐዋርያት እመቤታችንን ሊቀብሯት ሲወስዷት አዩ፡፡ ከዚያም በምቀኝነት «ቀድሞ ልጇ ሞቶ ተቀብሮ ሳለ ተነሣ ዐረገ እያሉ ሲያውኩን ነበሩ፤ አሁን ደግሞ እናቱን ሞታ ተነሣች እያሉ እንዳያውኩ ሥጋዋን እናቃጥል» ብለው በክፋት ምክር ተስማሙ፡፡ ወዲያውም እመቤታችንን አስክሬን ለማቃጠል ተነሣስተው ሔዱ፡፡

ከዚያም ታውፋንያ የሚባል ሰው ሐዋርያት ወዳሉበት ቦታ ቀረበና የእመቤታችን አስክሬን በሁለት እጆቹ በድፍረት ያዘው፡፡ ወዲያው የእግዚአብሔር መልአክ መጣና ታውፋንያ በድፍረት እጆቹን ዘርግቶ አስክሬኔን ስለያዘ እጆቹን በሰይፍ ቆረጠው፡፡ እጆቹም አልጋው ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ፡፡ ታውፋንያ እጁ በመቆረጡ ተጸጽቶ እመቤታችንን በድያለሁ ማሪኝ ብሎ በለመናት ጊዜ እጆቹ እንደ ቀድሞ ሆነው ዳኑለት፡፡

በመጨረሻም በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ መሠረት የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱስ ሥጋዋ ከወንጌላዊው ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር በገነት ውስጥ ከዕፀ ሕይወት ሥር በክብር ተቀመጠ፡፡ ከዚያም ቅዱሳን ሐዋርያት ዮሐንስ ከገነት ከተመለሰ በኋላ ‹‹እመቤታችን እንደምን አለች?›› አሉት፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም «ከገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አለች» አላቸው፡፡ እነርሱም ዮሐንስ አይቶ እኛ ሳናይ ብለው ነሐሴ አንድ ቀን ጾም ጀመረው ሁለት ሱባኤ ጾመው ሲጨርሱ በነሐሴ ፲፬ መልአኩ ቅዱስ ሥጋዋን ከገነት አምጥቶ ሰጥቷቸው በጸሎትና በምሕላ በክብር ቀበሩዋት፡፡ ከዚያም በሦስተኛው ቀን ተነሥታ በቅዱሳን መላእክት በታላቅ ሰማያዊ ዝማሬ ታጅባ ወደ ሰማይ ዐረገች፡፡

ታዲያ ልጆች! ከዚህ ጊዜ በኋላ ይህ በዓል ጥር ፳፩ ቀን የእመቤታችንን ዕረፍት ምክንያት በማድረግ በታላቅ ድምቀት በየዓመቱ መከበር ተጀመረ፡፡ እኛም በረከትን ለማግኘት ጥር ፳፩ ቀን አጥቢያችን በሚገኘው ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ቅዳሴ በማስቀደስ፣ ዝማሬ በመዘመር ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል እናከብራለን ማለት ነው፡፡ ቀደም ብለን በተነጋገርነው መሠረት በዓሉ አስተርእዮ ማርያም የተባለበት ምክንያት በጥር ወር ስለሚከበር ነው፡፡

በሉ ልጆች! ለዛሬ በዚህ ይብቃን፤ በሚቀጥለው በሌላ ታሪክ እስከምንገናኝ ደኅና ሰንብቱ፡፡ የእናታችን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነቷ ከሁላችን ጋር ይሁን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

# የሕፃናቱ ነገር

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ሕፃናት በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ልብ ያላቸው፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚፈጽሙ ደጋግ ሰዎች ሊይዙት የሚገባውን የዋህ ልብን ገንዘብ በማድረጋቸው ይታወቃሉ። ‹‹እውነት እላችኋለሁ፥ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም።›› /ማቴ ፲፰፥፫/ ያለው ቃሉ ለዚህ ምስክር ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በአእምሮ እንደ ሕፃናት አትሁኑ፤ ነገር ግን ለክፉ ነገር እንደ ሕፃናት ሁኑ›› /፩ኛ ቆሮ ፲፬፥፳/ በማለት ተናግሯል። ስለዚህ ሕፃናት የንጹሓን፣ የቅዱሳን፣ የጻድቃን ምሳሌ ሆነው የሚታዩ፣ በገርነታቸውና በየዋህነታቸው ነው።

ጌታችን በወንጌሉ ‹‹ሕፃናትን ተውአቸው፥ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና›› /ማቴ ፲፱፥፲፬/ ብሏል። ቀድሞም አገልጋዩ ቅዱስ ዳዊት የእነርሱን ዝማሬ እግዚአብሔር እንደሚቀበል ‹‹ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን ለራስህ አዘጋጀህ›› ብሎ ነበር። /ማቴ ፳፩፥፲፮/

ሕፃናት ከወላጆቻው ጋር እየተመላለሱ የበቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቅዱስ ቍርባን በመቀበል እና በመጠመቅ የበረከቱ ተካፋይ በመሆን በመንፈስ እያደጉ ይሄዳሉ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም ሀ ሁ…ብላ መልእክተ ዮሐንስ፣ ዳዊት እያለች ለማስተማር ቅድሚያ የምትወስደው ቤተ ክርስቲያን ነበረች። አስተምራም ዕድሜያቸው ከፍ ሲል ካህን የሚሆነው ዘልቆ በመማር ለክህነት፣ ንጉሥ ወይም ሀገር መሪ፣ ዳኛ ወዘተ. የሚሆነውም፣ ተጨማሪ ትምህርት በመማር የመንግሥት ሠራተኛ፣ አራሽ፣ ነጋዴ የሚሆነውም በየሞያው ተሰማርቶ ይኖራል። በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን በሕፃንነቱ የማትጎበኘው፣የማትዳስሰው፣የማትባርከው፣ የማታሳድገው የክርስቲያን ልጅ አልነበረም።

አሁን፣ አሁን ግን ዘመናዊ ትምህርት በሀገራችን መስፋፋቱን ተከትሎ ያለው የመንግሥት ሥርዓት ሕፃናቱ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ መሳቢያ የሚሆናቸውን ጥንታዊውን የትምህርት አካሔድ እንዳይሳተፉ የሚያደርግ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንን በአግባቡ ሳይተዋወቋት በጥምቀት፣ በሜሮን እና በቍርባን ብቻ ተወስነው የዓለማውያን ሐሳብ ብቻ እንዲሰፍንባቸው ሆነው እያደጉ ነው።

በዚህም ምክንያት አሁን አሁን በብዛት የኢትዮጵያ ተከታታይ ትውልድ ግብረ ገብን የማያውቅ፣ እግዚአብሔርን የማይፈራ፣ ጭራሽም የቤተ ክርስቲያንና የሀገርም አጥፊ የሚሆን ትውልድ እያፈራ መምጣቱን ማስተዋል ይቻላል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳር ተዘርግቶ ያለውን ወጥመድ መመከት የሚያስችል፣ ሕፃናትን የሚያቅፍ፣ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በሚፈለገው ደረጃ አለመዘርጋቱ ደግሞ አስተዛዛቢ ሆኗል። ሕፃናት ከባሕርያቸው ጋር በሚስማማ መልኩ በአገልግሎት ጊዜያት በቤተ ክርስቲያን እንዴት ይቆዩ ተብሎ ሥርዓት መሥራት ላይ መዘግየት ይታያል። ሕፃናት የሚታዩት እንደወላጆቻው ነው። ለወላጆቻቸው በተሠራ ሥርዓት እነርሱም በአገልግሎት ጊዜ ቆይታ እንዲኖራቸው ይደረጋል።

በአገልግሎት ጊዜያት ብቻ ሳይሆን በመዋቅር ደረጃ የሚያቅፋቸው አካልን ተጠያቂ የሚያደርግ ሥርዐት መኖሩ ያጠራጥራል። ሰንበት ትምህርት ቤቶች ለዚህ ኃላፊነት ያለባቸው ቢመስልም በተወሰኑት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ከሚደረጉ ውስን እንቅስቃሴዎች በስተቀር ለወጣቶቻቸው ከሚሰጡት ትኩረት ባሻገር ለሕፃናት የሚሰጡት አገልግሎት እየተስተዋለ ካለው ችግር አንጻር በቂ አይደለም።

የቤተ ክርስቲያንም አስተዳዳር ማወቅ የሚገባው ወሳኝ ቁም ነገር ምእመናን ከልጆቻቸው በላይ በሕይወታቸው ትኩረት የሚሰጡት ነገር አለመኖሩን ነው። በልጆቻቸው ምክንያት በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ ሕይወታቸውን እያሳለፉ መሆኑን ማስተዋል ይገባል። ይሄን አስተውሎ ከምእመናን ልብ፣ ሐሳብና ጭንቀት ጋር አለመጓዝ የቤተክርስቲያን አስተዳዳርን ከፍተኛ ትዝብት ላይ የሚጥለው ነው።

ወላጆች ወደ ቤተክርስቲያን የተለያዩ አገልግሎቶችን ፈልገው ሲመጡ ልጆቻቸውን ይዘው ይመጣሉ። እግዚአብሔርም ልጆቻቸውን እንዲባርክላቸው ይፈልጋሉ። ስለዚህ በምሥጢራት ያሳትፏቸዋል። ልጆቻቸውን ትተው ለመምጣት ቢፈልጉ እንኳን ልጆቻቸውን በቤት ትተው ለመመምጣት የሚቸገሩ ወላጆች ብዙ ናቸው። ሌላው ቀርቶ ወላጆች ልጆቻቸውን በሥራ ቦታዎቻቸው ላይ ይዞ የመገኘት ግዴታ ውስጥ በሚያስገባ የኑሮ ውጣ ውረድ ስለተያዙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጭምር የሕፃናት ማቆያዎችን በማዘጋጀት ከችግሮቻቸው ለማቅለል ሲሠሩ ይስተዋላል። ቤተ ክርስቲያን ግን ሕፃናቱ እንዲመጡ በብርቱ ትፈልጋለች፤ ሕፃናቱም በአንድም በሌላም መንገድ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው አልቀረም። ስለዚህ የሕፃናትን ባሕርይ ከግምት ያስገባ አቀባበል ማድረግ ያስፈልጋል።

ሕፃናቱን በቅዳሴ ጊዜ፣ በምሕላ ጊዜና በስብከተ ወንጌል ጊዜም ወላጆቻቸው ይዘዋቸው ሲመጡ እነርሱ በተለየ መንገድ የሚይዙበትን አካሔድ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንተከል ብሎ ማሰብ የዘመናችን የቤተክርስቲያን አስተዳዳር ግዴታ ነው። መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች እንዴት ይቀጥሉ፣ እንዴት ይስፋፉ፣ እንዴትስ ይደራጁ ብሎ ማሰብ ይገባል፤ የሰንበት ትምህርት ቤቶችን መዋቅርና አሠራርም እንዴት እናዘመን? እንዴትስ እንደግፍ? ብሎ መጠየቅ የክርስቲያች ግዴታ ነው።

ሕፃናቱ በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያንም ውጪ ቤተ ክርስቲያንን እንዲወዱ፣ ወደ እርሷም እንዲቀርቡ የሚያደርጉ የድምፅ ወምስል፣ የጽሑፍ ወዘተ. ዝግጅቶችን ማስፋፋት ያስፈልጋል። በዓለም ላይ ለሕፃናት ተብለው በኢ-አማንያን፣ በመናፍቃን የሚረጩ በኪነትና በቋንቋ ትምህርት ስም ከሚስፋፉ የድምፅ ወምስልና የጽሑፍ ሥራዎች ሕፃናትን ታድገን የቤተ ክርስቲያን ሆነው እንዲኖሩ ማድረግ የሚቻለው በአጸፋ በቂ ዝግጅቶች ሲኖሩ ነው። በዚህ ደረጃ ግን የቤተ ክርስቲያን መዋቅር አለመንቀሳቀሱ ትዝብት ላይ እየጣለው ነው።

በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት ቢያንስ በዘመናዊ ትምህርት ማስፋፋት ስም በመናፍቃን የሚሠሩ ደባዎችን ለማክሸፍ የጀመረቻቸው እንቅስቃሴዎች አበረታች ቢሆኑም በቂ አይደሉም። የቅዱስ ራጉኤል፣ የምስካዬ ኅዙናን፣ የአቡነ ጎርጎርዮስ ወዘተ. ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች መናፍቃን በዘመናዊ ትምህርት ስም ልጆቻችንን እንዳይወስዱ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ ሚና አላቸው። ነገር ግን እነዚህ ትምህርት ቤቶች ብቻ ችግር ሊቀርፉ አይችሉም። በክፍለ ሀገርም ተመሳሳይ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት አለባቸው። የቤተ ክህነቱ መዋቅር ይሄን በማበረታታትና በመምራት በኩል ንቁ ሊሆን ይገባል። በቤተ ክርስቲያን አቅምና መዋቅር ብቻ ሳይሆን ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች በምእመናናን ኅብረት፣ በአክሲዮን ወይም በግለሰብ ባለሀብቶችም እንዲስፋፉ ማድረግ ይገባታል። በዝቅተኛ ዋጋ፣ ወይም ያለዋጋ ክርስቲያን ሕፃናትን ሊያቅፉ የሚችሉ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች በበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ በድጎማ ወዘተ እንዲስፋፉ ማድረግም ሌላው አማራጭ ይሆናል።

ከላይ በዘረዘርናቸው ደረጃ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናትን እንድትታደግ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳር ካልተንቀሳቀሰ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠብቅ፣ ሀገሩን የሚወድ፣ በመልካም ሥነ ምግባር የታነጸ ትውልድ ማግኘት አይቻልም። በሰው ዘንድ ትዘብት ላይ ይወድቃል። በእግዚአብሔር ዘንድ ደግሞ የሚያስጠይቅ ይሆናል። ስለዚህ ሳይቃጠል በቅጠል ለማለት እንወዳለን።

# ትዳሬ ሊፈርስ ነው ምን የሻለኛል?

ክፍል አንድ

*ከባለቤቴ ጋር ከተዋወቅንበት ጊዜ ጀምሮም ይሁን በእጮኝነት ጊዜያችን፣ በየቀኑ ሳንተያይ ማሳለፍ የማይሆንልን፣ ሰዎችም የሚቀኑበት ፍቅር ነበረን። በኋላ በተክሊል ተጋባንና ኑሮ ጀመርን። አሁን ከተጋባን ዐሥር ዓመት ሆኖናል፤ በትዳር ቆይታችንም ሁለት ልጆችን አፍርተናል።*

*በጋብቻ ውስጥ ስንቆይ ግን፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ፍቅራችን እየቀዘቀዘ መጣ። በነገሮች አንግባባም፤ ተጣልተን እና ተኳርፈን የምናድርበት ቀናት እየበዙ፤ እርሷም ከዚህ በፊት ታሳየኝ የነበረው ፍቅርና አክብሮት ሁሉ እየቀነሰ ሄደ። እኔም ልጆቻችን በእኛ ምክንያት ተጽእኖ እንዳያድርባቸው እየፈራሁ ብዙ ዓመታት ታገሥሁ። አሁን ግን ነፍስ እያወቁ፣ ባለቤቴም ራሷን ማስተዳዳር የሚያስችላት ሥራና ደሞዝ ስላላት ብንፋታ የተሻለ ነው ብዬ አስቤያለሁ። ሌላ የማግባት ፍላጎት ኖሮኝ ሳይሆን ሰላም ለማግኘት በማሰብ ነው፤ ምናልባትም ለጸሎትና ለመንፈሳዊ ሕይወትም መልካም መንፈስ አገኛለሁ ብዬ አስባለሁ። እና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች ከእናንተ ምክርና አሳብ እሻለሁ፤*

ውድ ጠያቂያችን! ያነሡልን አሳብ በትዳር ሕይወት ውስጥ የሚታየውንና የሚከሠተውን ጉዳይ ነው። በእርግጥም፣ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ወደ ጋብቻ ለመምጣታቸው መሠረቱ ፍቅራቸው ነው። ያለ ፍቅር ወይም ያለ ፈቃድ ጋብቻ ሊመሠረት አይችልም። ቢመሠረትም እንኳን ለፈተና የተጋለጠ ይሆናል። ይልቁንም በክርስቲያኖች ዘንድ ሲመሠረት ስለፍቅር ከማሰብም በተጨማሪ ከፍተኛ ጥንቃቄና አስተዋይነት የእግዚአብሔር ፈቃድ መኖሩንም ታሳቢ መደረግ አለበት። ምክንያቱም ክርስቲያናዊ ጋብቻ የሚመሠረተው ለጊዜው በውስጡ ያለውን ፍቅር ብቻ ታሳቢ በማድረግ ሳይሆን በትዕግሥት፣ በመተሳሰብ፣ በመደጋገፍ ለመኖር ቃል ገብቶ የሚመሠርት ስለሆነ ነው።

የትዳር ሕይወት ሁል ጊዜ በምቹ ሁኔታ ላይራመድ ይችላል፤ እንደማንኛውም የክርስቲያኖች ሕይወት ገጽታ የሚፈተን የሕይወት ምዕራፍ ነው እንጂ። ስለዚህ ፍቅር ታላቅ ትዕግሥትን አዝሎ የሚጓዝ መሆኑን መገንዘብ ግዴታ ይሆናል፤ ሐዋርያውም ፍቅር ‹‹ይታገሣል›› ያለውን ልብ ይሏል።

ክርስቲያናዊ ጋብቻን በትኩረት ስናየው፤ክርስቲያኖች ያለ ዝሙት ምክንያት ወደ ፍቺ እንዳይደርሱ ፈጣሪያቸው ያዘዘበት ሕይወት ነው። ከሳ፤ ጠቆረ፤ ሰነፈ፤ ታመመ፤ መከነች፤ አጠረች፤ ከሳች፤ ጠቆረች፤ አጠፋች ወዘተ. ብሎ አንዱ በአንዱ አሳቦ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተፃሮ ጋብቻን ማፍረስ አልተፈቀደም።

እርስዎ እንደነገሩን ደግሞ የእናንተ ትዳር ለዐሥር ዓመታት ተጠብቆ የኖረና የሁለት ልጆች ወላጆች የሆናችሁበት የተከበረ ትዳር ነው። ብዙ የተጓዛችሁበት መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ ጋብቻ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ነገር ግን እርስዎ ችግር ያሉት የባለቤትዎ ፍቅርና ክብር መስጠት አለመቻል፣ በነገር አለመግባባትና መኮራረፍ የሰፈነበት ሁኖ ለፍቺ እየገፋፋዎት እንደሆነ ነግረውናል።

በእኛ በኩል ቅድሚያ ሰጥተን፣ ልናስገነዝብዎ የምንፈልገው ወሳኝ ነገር፣ እንዲህ ያሉ የትዳር ውስጥ ፈተናዎች በበርካታ ምእመናንን ሕይወት ውስጥ የሚንጸባረቁና በእርስዎ ትዳር ውስጥ ግን የበዛ፣ በሌሎች የሌለ አድርገው በማሰብ ከሰው የተለየ ነገር እንደደረሰብዎ አድርገው ከማሰብ እንዲቆጠቡ ነው። ትዳር እግዚአብሔር በዶኪማስ ቤት ተገኝቶ የባረከው በመሆኑ በተለያዩ ምክንያቶች ይፈተናል። የመጀመሪያው ነጥብ ግን በተጋቢዎች መካከል ግልጽነት የጎደለው ግንኙነት መስፈን ነው።

የበርካቶችን ትዳር ከአቅም በላይ የሚፈትኑት ግን የመካንነት ጉዳይ፣ የአመንዝራነት ጥርጣሬ፣ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት እና የመሳሰሉት ውስብስብ ችግሮች ናቸው። እርስዎ ከገለጹልን አሳብ አንጻር ግን በትዳርዎ ውስጥ የሚንጸባረቁት ፍቅርና ክብር ማጣት፣ በነገር ያለመግባባትና ኩርፊያ፣ ምናልባትም በትዳር ሕይወት ውስጥ ቀላልና ግልጽነት የተሞላበት ግንኙነት በመፍጠር ሊፈቱ የሚችሉ ፈተናዎች እንደሆኑ ማሰብ ይቻላል።

በጋብቻ ውስጥ ግልጽ የግንኙነት መርሕ፣ ቁልፍ የሆነ አዎንታዊ ሚና አለው። መነጋገርና መደማመጥም የትዳር መጠበቂያ መሣሪያዎች ናቸው። ምንም እንኳን የዘመናችን የኑሮ ውጣ ውረድ ጊዜ የሚያሳጣ፣ በድካምም የተሞላ ቢሆንም በተቻለ መጠን ግን ተጋቢዎች እርስ በእርስ ለመነጋገርና ለመስማማት ሰፊ አጋጣሚ፣ ጊዜና ሁኔታ

አላቸው። ትዳራቸው ዕድሜያቸውን፣ ሕይወታቸውን ሁሉ የሚሰጡበት የሕይወት ተቋማቸው በመሆኑ ሊነጋገሩ የሚችሉባቸውም ጉዳዮች በርካታ ናቸው። በመሆኑም የሚነጋገሩበት መንገድ ላይ ወደ ግጭትና ክርክር እንዳያመራ፤ ይልቁንም በተነሣው ጉይ ላይ ሊያስማማ እና ሊያግባባ የሚችሉ ጥበቦች ሊኖሩ ይገባቸዋል።

እንደተጋቢዎች አቅምና ግንዛቤም ንግግራቸው አንዳቸው በሌላቸው ላይ የሚፈጥረው ተጽእኖ ቀላል አይሆንምና ለይቅርታ ቦታ ለሚያጡ ተጣማሪዎች አንዲት ቃል ጦርነት እንዳታስነሣ ተጋቢዎች ከተጣማሪያቸው አንጻር አንደበቶቻቸውን መግራት ይጠበቅባቸዋል። በተለይ ጠብና ቊጣን የሚጭሩ ቃላትን ማዘውተር ለትዳር ጠንቅ መሆኑን መረዳት ይገባል። እንዲህ ያሉ ባለትዳሮችን ለማስጠንቀቅ ይመስላል ጠቢቡ ‹‹ጠበኛም ሚስት እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ ናት።›› ያለው /ምሳ ፲፱፥፲፫/። አንደበትን መግራት በየትኛውም ሕይወታችን ይጠቅማል፤ ትዳራችን ደግሞ ዋነኛው የሕይወታችን አካል በመሆኑ ከምን ጊዜውም በላይ ራሳችንን መግራት አለብን።

ስለዚህ ጠያቂያችን! በነገር አለመግባባት አንዱ ሌላውን በስክነት እና በፍቅር ካለማዳመጥ የሚመጣ ፈተና ሊሆን ይችላል። የባለቤትዎን ንግግር ብቻ ሳይሆን፣ የእርስዎንም በቀና መንፈስ ጆሮ የመስጠት ነገር አብሮ መመርመር ያስፈልጋል። መናገር ብቻ ሳይሆን የመስማት አቅምም በዚሁ ደረጃ የሚፈትን ነው። የተጣማሪን ቃል የምንተረጉምበትና የምንረዳበት ዐውዳዊ ሁኔታ አዘውትሮ የሚዛባ ከሆነ መግባባት አይኖርምና በሰከነ መንፈስ ማሰብ ያስፈልጋል።

ከዚህ አልፎም ባለቤትዎ በተለያዩ ምክንያቶች የማይገባ ነው ብለው የሚያስቡትን ቃል ሊናገሩ ይችላሉና ከሰው ድክመት እንደማይጠፋ ማሰብ አስፈላጊ ነው። ድክመትንና ስሕተትን በይቅርታና በትዕግሥት መሸከም ደግሞ የክርስቲያናዊ ጋብቻ ወሳኝ መርሕ ነው።

የትዳር አጋራችን ቢበድለንም፣ ባያስደስተንም እንኳን ወደ በጎው ነገር ለመመለስ በጸሎት ከመቆም ከማሰብ ኑሮአችንን ወደ መልካሙ ለማምጣት መጣር እንጂ ለመፋታት ማሰብ አይመከርም። ጋብቻን በፍቅርና በትዕግሥት መያዝ እንደሚገባንም መጽሐፍ ያስገነዝባል። ጠያቂያችን! ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስለሚስቶች በተናገረበት ዐውድ ውስጥ ‹‹እናንተ ሚስቶች ሆይ፥ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፥ በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው።›› /፩ጴጥ. ፫÷፩/ ባለው ቃል መሠረት ባለቤትዎ ሊማሩበት የሚችሉትን ትዕግሥትና መልካም ንግግር በማንጸባረቅ በፍቅር ለመገዛት መትጋት እንጂ ተማርሮ ወደ ፍቺ መጓዝ የሚመከር አይደለም።

የገቡበት ክርስቲያናዊ ጋብቻ /ትዳር/ ክርስቲያናዊ ሕይወት በመሆኑ መስቀሉን ተሸክሞ ክርስቶስን ለመከተል የተቀበሉት የኑሮ ቃል ኪዳን ነው። ከጋብቻ በኋላ የመፋታት ነጻነት አለን እያልን እንደ ዓለማውያን የምንኖረው ኑሮ አይደለንም። በጋብቻ ውስጥ ስንሆን አንዳችን በአንዳችን ሥር የታሰርን ነን እንጂ። በታላቅ ምሥጢርም አንዳችን የሌላችን ሥጋ ሆነናል። ስለዚህ ለክፋት የሚሆን አርነት በዚህ ውስጥ የለም። ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ።›› /፩ቆሮ. ፯፥፬/ ያለው ቃሉ በትኩረት መታወስ አለበት።

ስለዚህ አስቀድመን እንደተናገርነው፣ የተሻለውን ጋብቻን ለማጽናት የሚጠቅመው ፍቅርና ትዕግሥት ነው። በባለቤትዎ በኩልም የሚሹትን ፍቅርና ክብር የማግኘት ነገርን ለመመለስ በእርስዎ በኩል ማድረግ የሚገባዎትን በተሟላ ማድረግዎ ላይ አስቀድመው እርግጠኛ ይሁኑ። ሁል ጊዜም ከሌላው የምንጠብቅ ስንሆን ታዛቢ እንጂ የጋራ ሕይወት ይዳከማል። ሚስትዎ ለእርስዎ ማድረግ የሚገባትን ብቻ ሳይሆን እርስዎም ለሚስትዎ ማድረግ ያለብዎትን ሁሉ ማድረግዎትን ያረጋግጡ። ከነበረው ያጎደሉትን ማሰብ ያስፈልጋል፤ ሐዋርያው ‹‹ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት›› /፩ቆሮ. ፯÷፫/ ማለቱን ማስተዋል ነው።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ለሚቀዘቅዝ ፍቅር ምክንያቱ፣ ፍቅር ትኩስ እንዲሆን ስናደርግለት የነበረውን ጥቃቄና እንክብካቤ ስናጎድልበት ነው። የትዳር ሕይወት ብዙ ፈተናዎች ስላሉበት /በተለይ በአሁን ዘመን/ ትናንት ጋብቻ ሳይመሠረት ስናደርግ ከነበረው ያጎደልነው፤ ጋብቻ ከተመሠረተ በኋላ ልጆች ሳንወልድ ስናደርገው የነበረው፣ አሁን ልጆች ስንወልድ ያጎደልነው፤ ያቀዘቀዝነው ነገር ካለ ማጤን ያስፈልጋል።